# ጥናት አንድ ሐዋ ሥራ 18፡1-28 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ይህ ሃሳብ ሊጠቁመን የፈለገው ወደ ቆሮንቶስ ከመምጣቱ በፊት በአቴና አርዮስፋጎስ በተባለ ሥፍራ ከፈላስፋዎች ጋራ ወንጌልን ለመስበክ ያሳለፈውን ሁኔታ ለመናገር ፈልጎ ነው፡፡ ጳውሎስ በመጀመሪያ ያገኘው አቂላንና ጵርስቅላን ነው፤ እነዚህም ሰዎች ወደ ቆሮንቶስ የመጡት አይሁድ ሁሉ ከሮም እንዲወጡ ቀላውዲዎስ ባዘዘበት ወቅት ነው፡፡
2. ሲላስና ጢሞቲዎስ ከመምጣታቸው በፊት ከአይሁድና ከግሪክ ሰዎች ጋራ ነበረ አገልግሎቱ፤ እነርሱ ከመጡ በኋላ ግን ቁ5 እንደሚነግረን ያገለግል የነበረው ለአይሁድ እንደነበረ እናያለን፡፡ የጳውሎስ መልዕክት ትኩረቱ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ማወጅ ነው፤ ምክንያቱም አይሁድ ኢየሱስን መሲህና ክርስቶስ መሆኑን ለመቀበል ስላልቻሉ ነው፡፡
3. አይሁድ የሰጡት ምላሽ ተቃውሞና ስድብ የተሞላበት ሲሆን፤ ጳውሎስ ደግሞ በበኩሉ የወሰደው እርምጃ ራሱን በማራገፍ ደማቸው በራሳቸው ላይ እንዲሆንና እርሱ ንጹህ እንደሆነ ከአሁን በኋላ ደግሞ ወደ አህዛብ እንደሚሄድ ውሳኔውን ነገረ፡፡ ወንጌል ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ስላልሆነና ሌሎችም መስማት የሚገባቸው ሰዎች ስላሉ ወደ ሌሎች ዘወር የምንልበት ጊዜ ሊኖር እንደሚገባ እማራለሁ፡፡
4. ሰው ጥሩ ግብረገብ ስላለውና ህግን ስለሚያውቅ ለእውነተኛው ወንጌል ክፍት ነው ማለት እንዳልሆነና፤ በአንጻሩ ደግሞ ስለ እግዚአብሄር እውቀት የሌላቸውና በሃጥያት የሚኖሩ ለወንጌል የተዘጉ ናቸው ብለን ማሰብ እንደማይገባን እንማራለን፡፡
5. በቆሮንቶስ ከተማ ውስጥ ብዙ ነፍሳት እንዳሉት ገለጠለት(10)፡፡ ማበረታቻዎቹም፡ አትፍራ፣ ተናገር፣ ዝም አትበል፣ ከአንተ ጋራ ነኝ፣ ማንም ሊጎዳህ አይችልም፣ የሚሉት ናቸው፡፡ ያንን ያህል ጊዜ ለመቀመጥ እግዚአብሄር ከተናገረው ነገር አንጻር ይሆናል ብዬ እገምታለሁ፡፡
6. የምኩራብ አለቃ የነበረው ቀርስጶስና ቤተሰቦቹ፣(8)፣ስማቸውን የማናውቃቸው አምነው የተጠመቁት ብዙ የቆሮንቶስ ሰዎች(8)፣
7. ሶስቴንስ 1ኛ ቆሮንቶስ ሲጻፍ ከጳውሎስ ጋራ አብሮ የነበረ ወንድም ነው፡፡ አጵሎስ በመንፈስ የተቀጣጠለ፣ የጌታን መንገድ የተማረ፣ መጻህፍትን ጠንቅቆ የሚያውቅና የሚያስተምር ሰው እንደ ነበረ እንረዳለን፡፡ ጵርስቅላና አቂላ ደግሞ በቤታቸው ሰው የሚያስተናግዱና የጌታን መንገድ አውቀው የሚያሳውቁ ሰዎች ነበሩ፡፡
8. ብዙ መልካም ምግባር ያላቸው ሰዎች ቢገኙባትም በተክርስትያኒቱ አብዛኛው ጨቅላ፣ ክርስትና ያልገባው በመሆኑና በርኩሰትና በቅድስና መሃል ለመለየት ግድ ያልነበራቸው በመሆኑ ነው፡፡ በርኩሰት የሚመላለሱት በቁጥር መብዛታቸው ቤተ ክርስትያን የእግዚአብሄር መሆኗን አያስቀረውም፡፡

<u>ጥናት ሁለት 1ኛ ቆሮ 1፡1-17</u> (<u>ለመሪው የተዘጋጀ</u>)

1. ጳውሎስ በእግዚአብሄር ፈቃድ የክርስቶስ ኢየሱስ ሃዋርያ እንዲሆን የተጠራ እንደሆነ ይነግረናል፡፡ እኛም እያንዳንዳችን በተሰለፍንበት ሞያ ‹‹ለእግዚአብሄር ክብር አስተማሪ ለመሆን የተጠራ እገሌ››፣ ‹‹ለእግዚአብሄር ክብር ወታደር ሊሆን የተጠራ እገሌ›› እና የመሳሰሉትን ማለት እንችላለን፡፡ በዚህ ክፍል መሰረት የዚህች ቤተ ክርስትያን ባለቤት እግዚአብሄር ነው፡፡
2. እነዚህ ሁለት ስንኞች የሚያሳዩን ቤተ ክርስትያን በአንድ በኩል በአጥቢያ እንደ ቆሮንቶስ የተወሰነች ስትሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ጆግራፊ የማይወስናት በዓለም ዙሪያ ያሉትን ቅዱሳን ሁሉ የምታቅፍ ሰፊ እንደሆነች እንረዳለን፡፡
3. እግዚአብሄር ቅዱሳኑ ያለነቀፋ እንዲገኙ እስከመጨረሻው ድረስ አጽንቶ እንደሚጠብቃቸው ይነግረናል፡፡ የእግዚአብሄርም ታማኝነት በዚሁ ክፍል የተነገረበት ዋነኛው ምክንያት እርሱ አደርጋለሁ ያለውን ህይወታችን ያለነቀፋ እንዲገኝ ማድረጉን ጉዳይ ለመፈጸም እንደሚችል የሚናገር ብቻ ሳይሆን የሚያደርገው ታማኝ አምላክ መሆኑን ለመናገር ነው፡፡
4. እግዚአብሄር ቅዱሳኑን ወደ ልጁ ህብረት ጠራቸው ነው የሚለን፡፡ ቁ11-13ትን ስናነብ እነዚህ ሰዎች ለህብረት የተጠሩና የአንድነትን ነገር የሚያስተናግዱ እንዳልሆኑ እናያለን፡፡ ከዚህ አንጻር በዚህ ዘመን ያሉትን አብያተ ክርስትያናት ስናይ በብዙም የተለዩ ነው ብዬ አላምንም፤ ምክንያቱም የህብረትና የአንድነት ነገር ግድ የሚለን ብንመስልም ለአንድነትና ለሰላም መከፈል ያለበትን መስዋዕትነት ግን ለመክፈል ፈቃደኝነት አናሳይም፡፡
5. ሁሉም የሚያስቡት አንድ ይሁን ማለቱ ሳይሆን በፊሊ 2፡2-5 እንደምናነበው ሁሉም የክርስቶስ ዓይነት አስተሳሰብ እንዲኖራቸው፤ ማለትም ከራሳቸው ይልቅ ስለሰዎች እንዲያስቡ ማለቱ ነው፡፡
6. ለመከፋፈያነት የተጠቀሱት ስሞች፤ ጳውሎስ፣ ኬፋ፣ አጵሎስና ክርስቶስ ሲሆኑ ማናቸውም ቡድን በአሸናፊነት አልተጠቀሰም፤ ምክንያቱም ክርስቶስ አንድ ስለሆነና አካሉም አንድ እንጂ የተከፋፈለ ባለመሆኑ ነው፡፡
7. ክርስቶስ ተከፍሏልን? ጳውሎስ ለእናንተ ተሰቅሏልን? በጳውሎስ ስም ተጠምቃችኋልን? የሚሉት ሲሆኑ በዚህም ሊያስተምራቸው የፈለገው፤ የሁሉም ሰው ትኩረትና ትምክህት ክርስቶስ ብቻ መሆን እንዳለበት ነው፡፡ ጳውሎስ ይህንን ሲናገር ጥምቀት አያስፈልግም ማለቱ እንዳልሆነ የምናውቀው በመጀመሪያ ደረጃ ራሱ ተጠምቋል (ሥራ 9፡18)፣ አማኝ ሁሉ መጠመቅ እንዳለበት ያምናል (ሮሜ 6፡4)፡፡ ይህንን ያለበትን ምክንያት ክፍሉ ባይናገርም ምናልባት ሰዎች በእርሱ መጠመቃቸው ከሌሎቹ የበላይነት ስሜት እንዳያድርባቸው ለመጠንቀቅ ያደረገው ነገር ሊሆን ይችላል ብዬ እገምታለሁ፡፡
8. ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስትያን ችግር በመፍትሄነት ያገለገለው ሰው ለጳውሎስ የነበረውን ችግር ያስታወቁት የቀሎዔ ቤተሰቦች ናቸው እላለሁ፤ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ወሬን ተቀብሎ ወሬን ለሚያናፍስ ሰው ሳይሆን ለቤተ ክርስትያን ህይወቱን እንኳን ለመስጠት ፈቃደኛ ለሆነ ሰው ስለሆነ በዚህም ምክንያት እግዚአብሄር ድርጊታቸውን ባርኳል ማለት ይቻላል፡፡

# ጥናት ሶስት 1ኛ ቆሮ 1፡18-31 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሁለት ዓይነት ሰዎች ይታያሉ፡፡ እነዚህም የሚጠፉና፣ የሚድኑ ናቸው፡፡ ለሚጠፉት የመስቀሉ ቃል ሞኝነት ሲሆን ለሚድኑት ግን የእግዚአብሄር ሃይል ነው፡፡
2. በዚህ ክፍል በተደጋጋሚ የተጠቀሰው ቃል ‹‹ጥበብ›› የሚለው ሲሆን ይህ ቃል በእኔ አቆጣጠር ስምንት ጊዜ ያህል ተጠቅሷል፡፡ አንደኛው ሰማያዊ (የእግዚአብሄር) ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ምድራዊ (የሰው) ነው፡፡
3. ጥያቄዎቹ፡ ጠቢብ የት አለ? ሊቅስ የት አለ? ፈላስፋ የት አለ? እግዚአብሄር የዓለምን ጥበብ ሞኝነት አላደረገምን? ይህንን ማለቱ በዓለም ላይ የዚህ ዓይነት ሰዎች የሉም ለማለት ሳይሆን ደህንነትን በተመለከተ ይህ ሁሉ የትም እንደማያደርስ ለማሳየት ፈልጎ ነው፡፡ በነዚህ ቁጥሮች መሰረት የእግዚአብሄር በጎ ፈቃድ የሆነው ነገር፤ በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ማዳን ነው፡
4. በማቴዎስ ላይ ከጥበበኞች ሰወረ የሚለውን ሃሳብ ከ1ኛ ቆሮ 1፡20-25 ስናየው ጥበበኞች፣ አዋቂዎችና ፈላስፋዎች በገዛ ጥበባቸው ወደ እግዚአብሄር የመድረስ ጥረት እንደሚያደርጉ ነገር ግን እግዚአብሄር ማንም በራሱ እንዳይመካ ስለሚፈልግ በስብከት ሞኝነት ለመጡት ብቻ በሩን ይከፍታል፡፡ ከዚህ የምንማረው መጽሐፍ ቅዱስ ጠለቅ ብለን ካየነው በአብዛኛው ራሱን በራሱ የሚተረጉም መጽሐፍ እንደሆነ ማየት እንችላለን፡፡
5. በሰው ዓይን ሲታዩ ብዙዎች አዋቂዎች እንዳልነበሩ፣ ከትልቅ ቤተሰብ እንዳልተወለዱ፣ ሃያላን እንዳለነበሩ ያስታውሳቸዋል፡፡ እግዚአብሄር ደግሞ ጥበበኞችን ለማሳፈር የዓለምን ሞኝ ነገር እንደመረጠ፣ ብርቱዎችን ያሳፍር ዘንድ የዓለምን ደካማ ነገር እንደመረጠና የተከበረውን እንደሌለ ለማድረግ በዚህ ዓለም ዝቅ ያለውንና የተናቀውን ነገር እንደመረጠ ሲናገር ስላደረገበትም ምክንያት ሲናገር መንም ሰው በእርሱ ፊት እንዳይመካ ነው ይላል፡፡
6. ይህ ክፍል ክርስቶስን ጽድቃችን ሲል ከእግዚአብሄር ጋራ የምንታረቅበትና ተቀባይነት የምናገኝበት መሆኑን፣ ቅድስናችን ሲል ደግሞ ከዕለት ወደ ዕለት መቀደሳችን በእርሱ ሃይል እንደሆነና ቤዛነታችን መሆኑ ደግሞ የምንጠባበቀውን በሥጋ፣ በነፍስና በመንፈስ ሙሉ በሙሉ በማያዳግም ሁኔታ የምንድነው በእርሱ መሆኑን ይጠቁመናል፡፡
7. እዚህ ላይ ሶስት ዓይነት ሰዎች፤ አይሁዳዊያን፣ የግሪክ ሰዎችና፣ ሌሎቹ እኛ የሚለላቸው ደግሞ አይሁዶችንና የግሪክ ሰዎችን የሚጠቀልል ነው፡፡ አይሁድ ማየት የሚፈልጉት ተአምራትን ሲሆን የግሪክ ሰዎች ደግሞ ጥበብን ይሻሉ፡፡
8. እነዚህ ሰዎች የሚፈልጉትን አላገኙም፤ ምክንያቱም ለነርሱ ጥያቄ መልስ ሆኖ የቀረበላቸውና የሚሰበከው መልክክት የተሰቀለው ክርስቶስ ነው፡፡ በእነዚህ ሰዎች ዓይን ግን የተሰቀለው ክርስቶስ መሰናክልና ሞኝነት ሆኖ የሚታይ ሲሆን፤ ለሚድኑት ግን የእግዚአብሄር ሃይል እንደሆነ ይታያል፡፡

# ጥናት አራት 1ኛ ቆሮ 2፡1-16 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በቁ1-5 የምናያቸው ሁለት የስብከት መንገዶች እንዳሉ ሲሆን፤ አንደኛው በሚያባብል የጥበብ ቃል መስበክ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ የመንፈስን ሃይል በመግለጥ ይለዋል፡፡ ጳውሎስ የተጠቀመው የመንፈስን ሃይል በመግለጥ ማለትም የተሰቀለውን ክርስቶስ ሳይበርዝና ሳያመቻምች መስበክን ነው የመረጠው፡፡
2. ጳውሎስ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በተለያዩ መንገዶች በራሱ መመካት እንደማይችል አረጋግጧል፡፡ የረቀቀ የንግግር ችሎታና የላቀ ጥበብ አለመጠቀሙ፣ አመጣጡ ድካም፤ ፍርሃትና መንቀጥቀጥ የነበረበት መሆኑ፣ የሚያባብል ቃላት አለመጠቀሙና የመሳሰሉት በራሱ ሳይሆን ማዳን በሚችለው በእግዚአብሄር ላይ እንደታመነ እንመለከታለን፡፡
3. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሁለት ዓይነት ጥበቦችን እናያለን እነዚህም፤ የዚህ ዓለም ጥበብና፣ የእግዚአብሄር ጥበብ ተብለዋል፡፡ የእግዚአብሄር ጥበብ በባህርዩ ተሰውሮ የነበረ የእግዚአብሄር ምስጢር ነው፤ ከዘመናት በፊት ለክብራችን የተወሰነ ነው፣ የአለም ገዦች አልተረዱትም፣ ዓይን አላየውም፣ ጆሮ አልሰማውም፣ የሰው ልብ አላሰበውም፡፡
4. በእኔ አመለካከት በእነዚህ ሁለት ክፍሎች ላይ ስለሚናገራቸው ሰዎች ልዩነት አያለሁ፣ ይኸውም በቁ1 ላይ ያሉት ገና ያልበሰሉ፤ ቃሉን ቀላል በሆነ መንገድ መስማት የሚኖርባቸውና ጠለቅ ያለ የክርስትና እውነት ገና መረዳት የማይችሉ ሲሆኑ፣ በቁ6 ላይ የምንመለከታቸው ግን ከመጀመሪያ ትምህርት ያለፉ፣ የበሰሉና ጠንካራ ምግብን መመገብ የሚችሉ አይነት ሰዎች እንደሆኑ አያለሁ፡፡
5. ‹‹መንፈስ›› የሚለው ሲሆን፣ ዘጠኝ ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ እነዚህንም በሶስት ክፍሎ ነው ያሰፈራቸው፤ እነዚህም፡ የእግዚአብሄር መንፈስ፣ የዓለም መንፈስና የሰው መንፈስ በማለት ከፍሏቸዋል፡፡
6. በሁለት ክፍሎ ነው የሚያየው፤ አንደኛው መንፈሳዊ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ መንፈሳዊ ያልሆነ ወይም (ፍጥረታዊ) ሰው፡፡ ፍጥረታዊ ሰው መንፈሳዊ ነገርን መቀበል አይችልም፣ መንፈሳዊን ነገርን ደግሞ መረዳት አይችልም፡
7. ሀ) በሚያባብል የጥበብ ቃልና የመንፈስን ሃይል በመግለጥ መስበክ፣ ለ) የዓለም ጥበብና የእግዚአብሄር ጥበብ፣ ሐ) የዓለም መንፈስና የእግዚአብሄር መንፈስ፣ መ) መንፈሳዊ ሰውና ፍጥረታዊ ሰው ናቸው፡፡ በመጀመሪያው ላይ መንፈስ ቅዱስ ሃይሉን በመግለጥ(ቁ4)፣ ጥበብን አስመልክቶ የተሰወረውን በመግለጥ(ቁ10)፣ ሶስተኛው ደግሞ ስጦታችንን በማስታወቅ(ቁ12) አራተኛው ሃሳብ ላይ ደግሞ መንፈሳዊ ነገርን ለመመርመር በማስቻል(ቁ15)
8. ወንጌል ያለ መንፈስ ቅዱስ ሃይል ወደ ሰዎች ልብ ሊደርስ አይችልም(1ኛ ቆሮ 2፡4)፣ ለጠቢባን የተከደነውን ለሰዎች ይገልጣል(ቁ10)፤ ኢየሱስ ክርስቶስን ሙላት ያለእርሱ ማወቅ የለም፤ ያስችለናል(12)፣ ቃሉን ያስተምረናል(13)፣ ለሌሎችም እውነትን እንድናስተላልፍ ያስችለናል(13)፡፡
9. ያለ መንፈስ ቅዱስ ደህንነት የለም በሚለው ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ፤ በመጀመሪያ ደረጃ ተአምር በማድረግም ሆነ በማናቸውም መንገድ መጋረጃውን ከአይኖቻችን ባይቀድልን ለመንፈሳዊ ነገር እውሮች ሆነን በቀረን፤ ሌላው ደግሞ እንቅፋቱን ማስወገድ ብቻ ሳይሆን የደህንነትን ነገር መረዳት እንድንችል በቁ10 እንደተናገረው እውነቱን ባይገልጥልን ወደ ደህንነት የምንደርስበት ምንም መንገድ ባልኖረ ነበረ፡፡ ለዚህ ሁሉ የሚገባውን ምስጋናና አክብሮት ልንሰጠው ይገባናል፡፡

# ጥናት አምስት 1ኛ ቆሮ 3፡1-9 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ጳውሎስ የነበረበት ችግር ሊያስተላልፍ የሚፈልገው መንፈሳዊ እውነት ኖሮት ከሰዎቹ ብስለት ማነስ የተነሳ ማስተላለፍ አለመቻሉ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ግን አለመዳንን ያመለክታል በሚለው ሃሳብ በጭራሽ አልስማማም፤ ምክንያቱም ራሱ ህጻንነታቸውን ሲናገር በክርስቶስ በማለት ነው የጀመረውና ነው፡፡
2. እዚህ የምናያቸው ሁለት የምግብ ዓይነቶች፤ ወተትና ጠንካራ ምግብ በመባል ተጠቅሰዋል፡፡ የሰዎቹን የእድገት ደረጃና በመንፈሳዊ ህይወታቸው የት እንዳሉ ማወቁ ትክክለኛውን ዓይነት ምግብ ለመስጠት ረድቶታል፡፡
3. ከህጻንነት ባሻገር እነዚህ አማኞች ሥጋዊነት ሌላ ችግራቸው ነበረ፡፡ ለሥጋዊነታቸው መረጃ አድርጎ ያቀረበው ቅናትና ክርክር በመሃላቸው መኖሩን ነው፡፡
4. በቁ3 ላይ ‹‹ተግባራችሁስ እንደማንኛውም ሰው›› የሚለውና በቁ4 ላይ ደግሞ ‹‹ሰብዓዊ ፍጡር ብቻ መሆናችሁ አይደለምን›› የሚሉት ናቸው፡፡
5. ህጻን ክርስትያን፣ መንፈሳዊ ክርስትያን፣ ጠንካራ ክርስትያንናና ሥጋዊ ክርስትያን የሚሉት ናቸው፡፡
6. ቁ1-4 ያተኮረው በቆሮንቶስ ቅዱሳን ላይ ሲሆን፤ ቁ5-9 ደግሞ እያገለገሏቸው ባሉት አገልጋዮቻቸው ላይ ነው፡፡ በነዚህ ቁጥሮች ላይ ለቅዱሳኑ እድገት እየለፉ ያሉት፤ አጵሎስን፣ ጳውሎስንና እግዚአብሄርን እንመለከታለን፡፡ ከሶስቱም ሰራተኞች መሃል የበላይነቱ ሥፍራ የተሰጠው ለእግዚአብሄር ሲሆን፤ ምክንያቱም የሚያሳድገው እርሱ በመሆኑ ነው፡፡
7. ጳውሎስም ሆኑ አጵሎስ ምንም ማለት አይደሉም፤ ሁለቱም እንደተሰጣቸው ጸጋ መጠን የሚያገለግሉ አገልጋዮች ናቸው፤ ቅዱሳኑ ወደ እምነት እንዲመጡ መሳሪያ የሆኑ ናቸው፤ አንዱ ተካይ አንዱ ደግሞ አጠጪ ነበሩ፤ በተካይና በአጠጪ መሃል ብልጫ የለም፤ ሁለቱም እንደ ሥራቸው መጠን ሽልማት ይቀበላሉ፤ ሁለቱም የሚሰሩት ከእግዚአብሄር ጋራ ነው፡፡ የአገልግሎትን እኩልነት መረዳት ይጠቅማል ብዬ የማስብባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡ ሀ) የመድረክ ሽሚያን ባያስቀር እንኳን ይቀንሳል ለ) የበላይነትንና የበታችነትን ስሜት ያጠፋል ሐ) የሚችሉትን ያህል በትጋት ሰርቶ ውጤትን ለእግዚአብሄር መተው ይቻላል መ) ከሌሎች ጋራ ለመተባበርና አብሮ ለመስራት ትህትና ይፈጥራል፡፡
8. ከዚህ ጥቅስ የምረዳው ነገር ቢኖር፤ የአገልግሎት ሽልማት ለእያንዳንዱ ሰው እንዳለና ሽልማታችን ደግሞ እንደ ሥራችን መጠን እንደሆነ ነው፡፡ እንደ ሥራው ዓይነት ቢሆን መንፈስ ቅዱስ ራሱ ስለሆነ ስጦታዎቹን ሁሉ እንደፈቃዱ ያከፋፈለው በዓይነታቸው ብልጫ ያለው ዓይነት የተቀበሉት ሽልማታቸውም የበለጠ ይሆንና በዓይነታቸው ዝቅተኛ ተብለው የሚታሰቡትን የተቀበሉት ደግሞ ለአነስተኛ ሽልማት ራሱ መንፈስ ቅዱስ እንደወሰናቸው ይሆናል፤ ነገር ግን ማንኛውም ዓይነት ስጦታ ሆኖ የሽልማቱን ዓይነት የሚለየው የሰሪው ትጋትና ታማኝነት ነው፡፡

# ጥናት ስድስት 1ኛ ቆሮ 3፡10-23 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ጳውሎስ በእርሻው እንደ ተካይ ሲሆን በህንጻው ደግሞ መሰረትን ጣይ ሆኖ እናየዋለን፡፡ መትከልም ሆነ መሰረት መጣል ሁለቱም ጅማሬን የሚያመለክቱ ነገሮች በመሆናቸው የሚመሳሰሉበት ነገር አለ እላለሁ፡፡
2. ከነዚህ ዓይነት ንግግሮቹ መገምገም የምንችለው ምን ያህል በእርሱ ብርታትና ሃይል የእግዚአብሄር ሥራ እንደማይሰራ የተገነዘበ መሆኑን ነው፡፡ የግንባታው ሥራ የአማኝ ሁሉ ሲሆን፤ ማስጠንቀቂያው ደግሞ እንዴት መገንባት እንዳለብን መጠንቀቅ እንደሚገባን ነው፡፡
3. መሰረቱ ስለተጣለና መሰረቱ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ ነው፡፡ ማንም ሰው መሰረት መስርቻለሁ ብሎ ነገር ግን መሰረቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆኖ ካልተገኘ ድጋሚ መሰረት መጣል ግድ እንደሆነ አምናለሁ፡፡ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ 6 ዓይነት የግንባታ መሳሪያዎች ይታያሉ እነዚህም ወርቅ፣ ብር፣ የከበረ ድንጋይ፣ እንጨት፣ ሣርና አገዳ ናቸው፡፡
4. የአገልግሎታችን ጥራት በዚያን ቀን ለሁሉም ግልጽ ይሆናል፣ የእያንዳንዳችን ሥራ በእሳት ይፈተናል፣ ሥራችን በእሳቱ ውስጥ አልፎ ቢቆም ሽልማት እንቀበላለን፣ የሰው ሥራ ሁሉ ሊቃጠል የሚችልበት ሁኔታም ሊኖር ይችላል፡፡ ሥራው ከሰውየው ተለይቶ መቃጠሉ ሥራችን ወይም አገልግሎታችን ከደህንነታችን ጋራ የማይገናኝ ነገር እንደሆነ ያረጋግጥልናል፡፡
5. እግዚአብሄርና ቤተ መቅደስ የሚሉት ሲሆኑ፤ እነዚህም 5 ጊዜና 4 ጊዜ ተጠቅሰዋል፡፡
6. በጳውሎስ አነጋገር ቤተ መቅደስ የሚለው ሃሳብ በሶስት ዓይነት መንገዶች ሲጠቀም እንመለከታለን፡፡ እነዚህም ሀ) እያንዳንዱ ክርስትያን የእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ እንደሆነ (1ኛ ቆሮ 6፡19)፣ ለ) እያንዳንዱ አጥቢያ ቤ.ክ ቤተ መቅደስ እንደሆነ (1ኛ ቆሮ 3፡16) በመጨረሻም ሐ) ዓለም ዓቀፍ ቤ.ክ የእግዚአብሄር ቤ.መቅደስ መሆኑን ያሳያል (ኤፌ 2፡19-21)
7. ሶስት ዓይነት ሰዎች ይታያሉ፡፡ የመጀመሪያዎቹ በማይቃጠሉ ነገሮች የሚገነቡ፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ተቃጥለው በሚጠፉ ነገሮች የመገነቡና፣ በመጨረሻም ከመገንባት ይልቅ አፍራሽ ሰዎችን እንመለከታለን፡፡ በቁ16 ላይ የእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ መሆናችንን ሲናገር በዚያው ቁጥር ላይ የእግዚአብሄር መንፈስ በውስጣችሁ እንደሚኖር…የሚለው ማረጋገጫ ነው፡፡
8. ይህ የሚያጠቃልለው ሁሉንም አማኞች ሲሆን፤ ከቁ12 ጋራ የሚቃረነው ደግሞ እኔ የክርስቶስ ነኝ በማለት ሌላው የእርሱ እንዳልሆነ በሚያመለክት መንገድ ስለራስ ማሰብ ከሌሎቹ መከፋፈልን ካመጡት ስሞች የተለየ ሆኖ አይታይም፤ እያንዳንዱ አማኝ የክርስቶስ እንደሆነ ማሰብና መቀበል አስፈላጊ ነው፡፡
9. ጳውሎስ፣ አጵሎስ፣ ኬፋ፣ ዓለምም ሆነ ህይወት ወይም ሞት፣ አሁን ያለውም ሆነ ወደፊት የሚመጣው፣ ሁሉ የአማኝ ነው፡፡ በአንድ ሰው ላይ ብቻ ማተኮር የሚያስከትለው ትልቅ ችግር፤ እግዚአብሄር በሌሎቹ ወንድሞችና እህቶች ያስቀመጠልንን ብዙ የበረከት ዓይነቶች ሳናገኝ እንቀራለን ማለት ነው፡፡

# ጥናት ሰባት 1ኛ ቆሮ 4፡1-7 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ጸሐፊው ‹‹እኛን›› ብሎ ሲናገር ጳውሎስን፣ አጵሎስንና፣ ኬፋን ማለቱ ነው፡፡ ሁለቱ የአገልጋይ መለያ ሆነው ከተነገሩት አንደኛው የክርስቶስ ባሮች መሆናቸውና የእግዚአብሄር ምስጢር ባለ አደራዎች ናቸው፡፡ በ3፡22 ላይ ሁሉም የእናንተ ናቸው ሲባሉ ምናልባትም እነርሱን ለማገልገል ወይም እነርሱ የሚሹትን ለማከናወን ያሉ ሳይሆኑ ነገር ግን ለእነርሱ ጥቅም የተሰጡ ባርነታቸው ግን ለእነርሱ ሳይሆን ለክርስቶስ እንደሆነ ግልጽ ያደርገዋል፡፡
2. ቁ1 የተነገረው ለሰው ሁሉ ሲሆን በተለይም ለአማኞች ሁሉ ማለት ይቻላል፤ ቁ2 ደግሞ የወንጌል አደራ ለተቀበሉ አገልጋዮች በሙሉ ነው፡፡ ባለ አደራዎች ታማኝ ሆኖ መገደኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ታማኝነት ሲል ከአውደ ምንባቡ አንጻር ወንጌል ለሚለው ነገር ወዲያና ወዲህ ማመቻመች እንደማይኖርበትና የአደራ ነገር ስለሆነ የተሰጠውን ብቻ መስጠትን እንደሚመለከት አስባለሁ፡፡
3. የተደጋገመው ቃል ፍርድ የሚለው ሃሳብ ነው፡፡ የቆሮንቶስ ክርስትያኖች፣ ሰዎች በአጠቃላይ፣ ራሱ ጳውሎስና፣ ጌታ ናቸው፡፡ ጌታ ብቻ በእርሱ ላይ የመፍረድ ብቃት እንዳለው ነው የሚያምነው፤ ምክንያቱም በጨለማ የተሰወረውንና በሰው ልብ ውስጥ ያለውን ሁሉ ስለሚያውቅ ነው፡፡
4. ምክንያቱም ጳውሎስ የአስተሳሰቡን (Motive) ንጹህነት ሙሉ በሙሉ ማወቅ አይችልም፡፡ ህሊና በአብዛኛው ትክክል የሚጠቁመን ሲሆን ነገር ግን ከዚህ ክፍል የምንረዳው ምን ያህል በህሊናችን መቶ በመቶ መተማመን እንደማንችል፡፡
5. 1ኛ ቆሮ 5፡12 በተገለጠ ሃጥያት ላይ፣ 1ኛ ቆሮ 6፡1-5 በቁጹሳን መሃል በሚነሳ አለመግባባት ላይ፣ 1ኛ ቆሮ 10፡15 ሰዎች የሚናገሩትን በሚናገሩት ንግግር ላይ መፍረድ እንችላለን፡፡ በ1ኛ ቆሮ 4 ላይ የተከለከለው ፍርድ የሰዎችን ውስጣዊ አስተሳሰብ ማለትም ሰውየው እንኳን (ጳውሎስ) ለማወቅ የሚቸገረውን ነገር ከመፍረድ እንድንጠበቅና ለጌታ እንድንተውለት ተነግሮናል፡፡
6. በጨለማ የሚደረግ ወይም በድብቅ የሚደረግ ነገርና በልብ ውስጥ ያለ ነገር ናቸው፡፡ የእነዚህ ነገሮች ፍርድ ጌታ ሲገለጥ ነው፡፡ ይህ አነጋገር እኛ ብንፈርድ ለአብዛኞዎቹ ሰዎች የማይገባቸውን ብያኔ እንደምንሰጣቸው ይጠቁመናል፡፡
7. ‹‹ከተጻፈው አትለፍ›› የሚለውን ከእኛ እንድትማሩ ነው ይላል፡፡ ምናልባትም ሊሆን እንደሚችል ከአነጋገሩ እረዳለሁ፡፡ መከፋፈልን በተመለከተ ማጠቃለያ ሃሳቡ በቁ6 ላይ የተናገረው ‹‹አንዱን ሰው ከሌላው አብልጣችሁ አትመኩበት›› የሚለው ነው፡፡
8. እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ በማካፈል ተወያዩበት፡፡

## ጥናት ስምንት 1ኛ ቆሮ 4፡8-21 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እነዚህ ሰዎች የሚያስፈልገን ነገር ሁሉ አለን የሚሉ፣ ሃብታሞች ነን የሚሉና እንደ ንጉሥ ራሳቸውን የካቡ ሰዎች እንደሆኑ ማየት ይቻላል፡፡ በቁ7 ላይ ከሌላው በልጠው ቢሆን ለዚህ ማን ለዚህ አበቃችሁ? አለኝ የምትሉ ከሆነ ምንጩ ጌታ መሆኑን ዘንግታችኋል ወይ? አይ ጌታ ነው የሰጠኝ የምትሉ ደግሞ ከሆነ ትምክህትን ምን አመጣው? በማለት ነው የሚጠይቃቸው፡፡
2. አንዳንድ ጊዜ ሃዋርያቱን እግዚአብሄር ሞት እንደተፈረደባቸው ሰዎች ከሰው ሁሉ መጨረሻ ያሰለፋቸው ሆኖ ይሰማዋል፤ ለዓለም ሁሉ መላዕክትም ለሰዎችም ትርዒት እንደሆኑም ይሰማዋል፡፡ ሐዋርያቱ ከቆሮንቶስ ሰዎች ጋራ ሲያነጻጽር፤ እኛ ሞኞች እናንተ ግን ጥበበኞች፣ እኛ ደካሞች እናንተ ግን ብርቱዎችና፣ እኛ የተዋረድን እናንተ ግን የተከበራችሁ በማለት ያነጻጽራል፡፡
3. እንራባለን፣ እንጠማለን፣ እንራቆታለን፣ እንደበደባለን፣ ያለመጠለያ እንንከራተታለን፣ በገዛ እጃችን እየሰራን እንደክማለን ይላል፡፡ ሁሉም አማኝ ባለጠጋ እንዲሆን የእግዚአብሄር ፈቃድ ነው በማለት እግዚአብሄርን መምሰል ማትረፊያ አድርገው ለሚናገሩ ከሃዋርያቱ የበለጠ መንፈሳዊነት አለኝ ካላሉ በስተቀረ እነርሱ እየተለማመዱ ያሉት ጥማት፣ ራቁትነት፣ ረሃብና የመሳሰሉትን ነው፡፡
4. ሲረግሚቸው ይመርቃሉ፣ ሲያሳድዷቸው ይታገሳሉ፣ ስማቸው ሲጠፋ መልካም ይመልሳሉ፡፡ እነዚህን ሶስት ጥቅሶች በማመሳከር ሃዋርያቱ የኖሩት እንደ እግዚአብሄር ቃል እንደነበረ ሙሉ በሙሉ ያረጋግጡልናል፡፡
5. እነዚህ ሰዎች እንደ እግዚአብሄር ቃል ይኑሩ እንጂ የነበሩበት ሁኔታ ምንም አልተቀየረም፤ ምክንያቱም በቁ13 መጨረሻ ላይ እስከ እሁንም ድረስ የዓለም ጉድፍ እንደሆኑና የምድርም ጥራጊ ሆነው እንደሚቆጠሩ ይናገራል፡፡ ከሃዋርያቱ ህይወት መማር የምንችለው ነገር፤ እግዚአብሄርን መታዘዛችን ሁኔታዎቻችን እንዲቀየሩልን ሳይሆን የእኛን ሃጥያተኛ ልብ ስለቀየረን የፍቅራችን ምላሽ አድርገን ልናየው ይገባናል፡፡
6. ጳውሎስ አባታቸው እነርሱ ደግሞ ልጆቹ እንደሆነ የምናይ ሲሆን ይህም ግንኙነት የተፈጠረው በወንጌል የወለዳቸው ስለሆነ ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት እርሱን እንዲመስሉ ያበረታታቸዋል፡፡
7. በጌታ የተወደደ፣ የታመነና ጳውሎስ በወንጌል የወለደው ልጁ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ ጢሞቲዎስ ወደ ቆሮንቶስ የተላከው ጳውሎስን በመሃላቸው ሳለ የተመላለሰውን ህይወት እንዲያሳስባቸው ነው፡፡ ለአገልግሎቱ ሃይል የሚሰጠው ነገር ትምህርቱና አካሄዱ አንድ የመሆናቸው ጉዳይ ነው፡፡
8. ወሬ ወይም ቃልን ብቻ ስለተሞሉ እንጂ የወንጌል ሃይል ውስጣቸውን ስላልቀየራቸው ሰዎች ነው፡፡ ይህ ሃይል የሚለው ሃሳብ በመንፈስ አማካኝነት ወንጌል በሰዎች ውስጥ የሚሰራው ሥራ ይሆናል፡፡
9. የጳውሎስ ህይወት የወንጌልን እውነት በቃል ወይም ወሬው ብቻ ሳይሆን አካሄዱ የሚመሰክርለት በመሆኑ ነው፡፡

# ጥናት ዘጠኝ 1ኛ ቆሮ 5፡1-13 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በተለይ ‹‹እንዳለ›› የሚለው ሃሳብ አንድ ጊዜ ተደርጎ የቆመ ነገር ሳይሆን አሁንም ያለና የሚካሄድ ቋሚ ነገር እንደሆነ ይጠቁመናል፡፡ አህዛብን ወይም አረማውያንን እንኳየሚያስደነግጥ የሃጥያት የሃጥያት አይነት መሆኑ ነው፡፡
2. የጌታ ስም በመጉደፉ፣ የዚህ ሰው ህይወት በመበላሸቱና ለቤተ ክርስትያን መሰደቢያ በመሆኑ፣ በጌታ ህጻናት ለሆኑትና በውጭ ላሉት እንቅፋት በመሆኑ… ወዘተ፡፡
3. ስብሰባው የሚያጠቃልለው የቆሮንቶስ ቤተ ክርስትያንን ምዕመናን፣ ጳውሎስ በመንፈስ እና ኢየሱስ ክርስቶስን ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በግል መምከርን፣ ሁለት ወይም ሶስት ሆኖ ማነጋገርንና በቤተ ክርስትያን ምዕመናን መመከርን አልፎ የመጨረሻው ደረጃ ላይ እንዳለ እገምታለሁ፤ ምክንያቱም እዚህ ሥፍራ ላይ ለሰውየው ምንም ዓይነት ተጨማሪ ነገር እንዲደረግለት ሳይሆን ከጉባኤው እንዲወገድ ነው ውሳኔው፡፡
4. ተሰብሳቢዎቹ ሊወስዱት የሚገባቸው ቆራጥ እርምጃ ይህንን ያደረገው ሰው ለሰይጣን አልፎ እንዲሰጥ ማድረግ ነው፡፡ ይህንን ውሳኔ ሲወስኑ አማኞቹ ግባቸው ሊሆን የሚገባው ነገር ይህንን ያደረገው ሰው ሥጋው እንዲጠፋና መንፈሱ ግን በጌታ ቀን እንዲድን ነው፡፡ ውሳኔው ተፈጻሚነት እንደሚያገኝ እርግጠኛ ሊያደርጋቸው የሚችለው ኢየሱስ ክርስቶስ በመሃላቸው መገኘቱ ነው፡፡
5. በነዚህ ቁጥሮች ላይ ምክንያት ሆኖ የቀረበው ነገር ጥቂቱ እርሾ ብዙውን ሊጥ ሊያቦካ እንደሚችል የዚህ አይነቱ ሃጥያትም ዝም ከተባለ ቤተ ክርስትያንን በሙሉ ሊበክል ይችላል ማለት ነው፡፡ እርሾ በዚህ ክፍል መሰረት ሃጥያትን የሚያመለክት ነው፡፡ ያለ እርሾ መሆን የሚኖርብን ዋና ምክንያት ፋሲካችን የሆነው ክርስቶስ ስለተሰዋልን ነው፡፡
6. ‹‹በመልዕክቴ ጽፌላችሁ ነበር፡፡›› የሚለው በእግዚአብሄር ቃል ላይ የሰፈረ ነገር መሆኑ ሌላ ጠንካራ ምክንያት ይሰጣቸዋል፡፡ ማብራራት የፈለገው ነገር ከሴሰኞች ጋራ አትተባበሩ ሲል ያላመኑትን ሰዎች እንደማይጠቀልልና በቤተ ክርስትያን ውስጥ ሆነው የተለያዩ ሃጥያቶችን ኑሮዮ ብለው የተያያዙትን ሰዎች የሚመለከት እንደሆነ ያብራራላቸዋል፡፡
7. የዚህ አይነት ሰው ህይወቱ በምንም መንገድ የክርስቶስ መሆኑን ስለማይመሰክር ወንድሜ ብሎ ለመቀበል አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ የየግሉን ሃሳብ ይናገር፡፡ ሰውን ወንድሜ ወይም ክርስትያን ነው ብሎ ለመናገር የሚያስቸግረው የየእለት አኗኗሩ ክርስትናውን የማያመለክት ሲሆን ይህ ችግር ይኖራል፡፡
8. ፍርድን አስመልክቶ ሰዎችን በሁለት ከፍሏቸዋል፤ እነዚህም ከቤተ ክርስትያን ውጭ ያሉና በቤተ ክርስትያን ውስጥ ያሉ ናቸው፡፡ ይህም ሰው በቤተ ክርስትያን ውስጥ የነበረ ሰው ነው፡፡
9. ውሳኔያቸውን ተፈጻሚ ለማድረግ የሰይጣን አስተዋጽዖ የሰውየውን ሥጋ ማጥፋት ነው፡፡ እነዚህ ጥቅሶች የሚያሳዩኝ ምን ያህል እግዚአብሄር በሰይጣን ላይ እንኳን ቁጥጥር እንዳለው ነው፡፡

# ጥናት አስር 1ኛ ቆሮ 6፡1-8 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በመካከላችሁ ሲል በቤተ ክርስትያኒቱ ውስጥ ማለቱ ነው፡፡ በቆሮንቶስ ሰዎች መሃል የተከሰተው ችግር እርስ በእርስ ሙግት መኖሩ ሲሆን፤ ጳውሎስን ያሳሰበው ነገር ችግሩ መኖሩ ሳይሆን ለችግሩ የተወሰደው መፍትሄ ነው፤ ማለትም በአማኞች መሃል ማለቅ ሲገባው ወደ አህዛብ መሄዱ ነው፡፡
2. በዓለም ላይ ለመፍረድ የሚበቁ ከሆነ ለዚህ ዓይነቱ ነገርማ ያለጥርጥር መብቃት አለባቸው የሚል ይመስላል፡፡ ‹‹ትንሹ ነገር›› ሲል ከዘላለሙ ጋራ ሲወዳደር ትልቅ የተባለው ሁሉ ምናምንቴ ሆኖ ይገኛል፡፡
3. እንዲያውቁ የሚጠበቅባቸው አንደኛው ቅዱሳን በዓለም ላይ እንደሚፈርዱና ሌላው ደግሞ ቅዱሳን በመላዕክት ላይ እንደሚፈርዱ ነው፡፡ ይህንን መረዳት መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው ስለሚኖር እነርሱ ካላመኑት በተሻለ በጽድቅ የመፍረድ ብቃት ያላቸው መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል፡፡
4. ከፍርድ ቤት ይልቅ በአማራጭነት ጳውሎስ የሚያቀርበው ነገር እርቅን ማድረግ ነው፡፡ በዚህ ምንባብ መሰረት ለማስታረቅ ጥበብ ወይም አስተዋይ ሰው ይጠይቃል፡፡
5. ጳውሎስ በዚህ ምንባብ ውስጥ ፍርድ ቤት መኖሩን እየተቃወመና ፍርድ መካሄድ ያለበት በቤተ ክርስትያን ውስጥ ብቻ መሆን አለበት እያለ አይደለም፤ ምክንያቱም ሮሜ 13ትን ስናነብ የዚህ ዓይነት ሃሳብ እንደሌለው በግልጽ እንመለከታለን፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ሊናገረን የፈለገው ዋነኛው ሃሳብ አማኞች በመሃላቸው ለሚነሳው ማናቸውም አይነት አለመግባባት ወደ አህዛብ ሳይወጣ በራሳቸው መጨረስ እንደሚኖርባቸው ለማስተማር ነው፡፡
6. እነዚህ ሰዎች በፍርድ ረትቻለሁ ቢሉም እንኳን በመንፈሳዊ ረገድ የክርስቶስን ስም መሰደቢያ፣ አካሉ የሆነችው ቤተ ክርስትያንም መሳለቂያ በማድረጋቸው ቢረቱም ተረተዋል፤ በዚህ ሁለቱም ተረቺዎች በሆኑበት ውስጥ አሸናፊ ሆኖ የሚገኘው የነፍሳችን ጠላት ሰይጣን ብቻ ነው፡፡
7. የጳውሎስ ምክር በአጭሩ ለክስ ከምትሄዱ ተበድላችሁም ሆነ ተታላችሁ እንዳላወቀ ሆናችሁ ብታልፉት ይመረጣል ይላቸዋል፡፡ ይህ ክፍልም ሆነ በማቴዎስ ላይ ያለው ጥቅስ ሁለቱም መብታችን እንደሆነ በምናውቃቸው ነገሮች ላይ እንኳን ለጌታ ብለን ጉዳትን ለመቀበል ፈቃደኛ መሆንን ያስተምሩናል፡፡
8. መብቱን በመተው አምላክነቱን ትቶ ለውርደት፣ ለስድብና ለሞት ራሱን የሰጠው የእኛ ምሳሌ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

# ጥናት አስራ አንድ 1ኛ ቆሮ 6፡9-20 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በቁ9 መሰረት አማኞች እንዲያውቁት የሚጠበቅባቸው ነገር ዐመጸኞች የእግዚአብሄርን መንግሥት እንደማይወርሱ ነው፡፡ በቁ7 ላይ አውቀን እንዳላወቀ በመሆን መብትን ከመተው አኳያ ሲሆን፣ በቁ9 ዐመጻን አስመልክቶ ግን ልንታለልም ሆነ ራሳችንን ልናታልል እንደማይገባን ነው የሚነግረን፡፡
2. ሃሳቡ የሚያመለክተን የሃላፊን ጊዜ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ስለሚገኙበት ሁኔታ የሚነግረን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እንደታጠቡ፣ እንደተቀደሱና፣ እንደጸደቁ ይነግረናል፡፡
3. እግዚአብሄር በዚህ ዓይነት ህይወት ለመኖር ለቆረጡት መንግሥቱን ከማይወርሱት ውስጥ ይመድባቸዋል፡፡ በቁ11 ደግሞ ከቆሮንቶስ ሰዎች አንዳንዶቹ የነዚህ ዓይነት ሰዎች እንደነበሩና ዘሬ ግን ሌላ ህይወት እንደሚለማመዱ ስናይ ለማንኛውም ሰው የዚህ ዓይነት ተስፋ እንዳለ፤ ወደ ጌታ በመምጣትም ከርኩሰት መታጠብ፣ መቀደስና መጽደቅ እንዳለ አያለሁ፡፡
4. ሁለቱ መመሪያዎች፤ ተፈቅዶልኛል ወይስ አልተፈቀደልኝም? ሳይሆን፤ ጥያቄያችን ሊሆን የሚገባው ለእድገቴ ይጠቅመኛል ወይስ እድገቴን ያስተጓጉልብኛል?፣ ሌላው ደግሞ በነጻነት እንድመላለስ አስተዋጽዖ ያደርጋል ወይስ ለባርነት ይዳርገኛል የሚሉት ናቸው፡፡
5. በቁ13 ላይ ጳውሎስ የሚነግረን ነገር፤ ምግብ ለሆድ እንደሆነና ሆድም ለምግብ መሆኑን ነው፡፡ በዚህ አነጋገሩ ሊያስረዳን የፈለገው እውነት፤ እነዚህ ሁለቱ ነገሮች ጊዜያዊ እንደሆኑና ጊዜያችንን ሁሉ ለሆዳችን የሚሆነውን ብቻ በማሳደድ እንዳናሳልፈው ያስገነዝበናል፡፡
6. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በብዛት የተጠየቀው ጥያቄ ‹‹…አታውቁምን?›› የሚል ሲሆን ጥያቄው አራት ጊዜ ተጠይቋል፡፡ ከነዚህ ከአራቱ ውስጥ ሶስቱ ከሰውነታችን ጋራ በተያያዘ የተጠየቁ ናቸው፡፡
7. በቁ18 ላይ መፍትሄ ሆኖ የተነገራቸው ነገር ከዝሙት እንዲሸሹ ነው፡፡ በሰውነታችን እግዚአብሄርን ማክበር የሚገባን፤ አንደኛ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ስለሆንና ሁለተኛው ደግሞ በዋጋ ስለተገዛንና የራሳችን ስላልሆንን ነው፡፡ 1ኛ ቆሮ 3፡16 የእግዚአብሄር መቅደስ ሲለን 6፡19 ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ መቅደስ ስለሚል፤ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሄር መሆኑን ያረጋግጥልናል፡፡
8. በቁ11 ላይ መንፈስ ቅዱስ የሰራው ስራ፤ ሰዎችን ማጠብ፣ መቀደስና፣ ማጽደቅ ነው፡፡ ይህንንም ሥራ ከተሰራባቸው መሃል ለመጥቀስ፤ በቁ9-10 የሚገኙትን ሁሉ ሁሉ መጥቀስ ይቻላል፡፡ አዎን ‹‹ከእናንተ አንዳንዶቻችሁ እንደዚህ ነበራችሁ›› ሲል ግብረ ሰዶማውያንንም ጭምር ማለቱ ነው፡፡

## ጥናት አስራ ሁለት 1ኛ ቆሮ 7፡1-11 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የቀደሙት ምዕራፎች ሰዎች በነገሩት ሁኔታዎች ላይ ተመርኩዞ የጻፈው ሲሆን፤ ከዚህ በኋላ ግን በምዕመናኑ በተጠየቀው ጥያቄዎች ላይ ያተኮረ ነው፡፡
2. የዝሙት ርኩሰት እየበዛ በመሄዱ ነው፡፡ ሁለቱ የሚያፈርሳቸው ሃሳቦች፤ አንደኛው ወንድ ከወንድ ጋራ የሚለውን አመለካከትና ሁለተኛው ደግሞ አንድ ወንድ ከአንድ ሴት እንጂ ከአንድ በላይ ለሚለውም ትክክል አለመሆኑን ይጠቁመናል፡፡
3. እነዚህ ቃላት የሚናገሩት ስለግብረ ሥጋ ግንኙነት ጉዳይ ነው፡፡ የባል ሰውነት የሚስትም ጭምር ሲሆን፤ የሚስት ሰውነት ደግሞ የባሏም ጭምር ነው፡፡ ሰውነቱ የራሱ ብቻ እንዲሆን የሚፈልግ ሰው ከመጀመሪያው ማግባት አይኖርበትም፤ ካገባ ግን ሌላ ምርጫ የለውም፡፡
4. አዎን እላለሁ፤ ይህንን ማለት የቻልኩት ጸሃፊው ‹‹ሰይጣን እንዳይፈትናችሁ እንደገና አብራችሁ ሁኑ›› ስለሚል ጠላት ያንን እድል ለመጠቀም ዝግጁ እንደሆነ ኢያለሁ፡፡ ባለትዳሮቹ ይህ እንዳይሆን የተመከሩት ምክር ተለያይተው እንዳይቆዩና፣ ከተለያዩም ደግሞ ቶሎ አብረው ወደመሆን እንዲመለሱ ነው፡፡
5. ጳውሎስ በዚህ ክፍል ሰው ሁሉ እንደርሱ ቢሆን ይመኛል፡፡ ይህንን ሲል ሰው ሁሉ እንደ እርሱ ሳያገባ ቢኖር እንደሚሻል ለመናገር ነው፡፡ ተጨባጩ ሁኔታ ሰው ሁሉ እንደ ጳውሎስ መሆን እንደማይችል ሲሆን ምክንያት ሆኖ የተሰጠንም እንደእርሱ መሆን ከእግዚአብሄር ስጦታ ሆኖ እንደሚሰጥና ያለበለዚያ ግን ማግባት እንደሚሻለን ይመክረናል፡፡
6. ይህንን ሲል ጌታ ራሱ በወንጌላት ላይ አጥብቆ የተናገረው ሃሳብ እንጂ እኔ አዲስ የተቀበልኩት ቃል አይደለም ለማለት ነው፡፡ በአንድ ቃል ‹‹አትፋቱ›› እለዋለሁ፡፡ የመለያየቱ ሁኔታ ግድ ሆኖ ከተለያዩ ያሏቸው ሁለት አማራጮች ሳያገቡ መኖር ወይም መታረቅ ናቸው፡፡
7. ከመስማማት የሚቀድመው ነገር መነጋገር ወይም መወያየት ነው እላለሁ፡፡ በአንድነት እንዲያደርጉ የሚጠበቅባቸው ሁለት ነገሮች ደግሞ የመጀመሪያው በሁለቱ መሃል ውይይትና የሃሳብ መለዋወጥ ሊኖር እንደሚገባና  በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የቤተሰብ ጸሎት መኖር እንዳለበት እናያለን፡፡
8. ያለነዚህ ሁለት ነገሮች ትዳርን በትክክለኛ መንገድ ለማቆም እጅግ አዳጋች እንደሚሆን አልጠራጠርም፤ ምክንያቱም አብዛኛው ችግር የሚፈጠረው በነገሮች ላይ መነጋገርና የጋራ የሆነ መስማማት ስለማይኖር ሲሆን ሌላውና ዋነኛው ችግር ደግሞ በአንድነት በጌታ ፊት የሚቀረብበት ምንም ዓይነት የጸሎት ጊዜ ባለመኖሩ ነገር ሁሉ የመዘበራረቅ ሁኔታ ይኖረዋል እላለሁ፡፡

# ጥናት አስራ ሶስት 1ኛ ቆሮ 7፡12-24 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ከነዚህ ሰዎች በተጨማሪ ለሶስት ዓይነት ሰዎች ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ሁለቱም አማኞች ለሆኑ፣ (1-7) ላላገቡ (8)፣ አግብተው ለሞተባቸው (8)፣ ተጋብተው ችግር ላለባቸው (10)፡፡ ይህንን አነጋገር የምረዳው በቁ10 ላይ ጌታ የተናገረው ላይ በመመርኮዝ እንደተናገርኩት ሳይሆን ይህ አስቀድሞ ያልተሰጠ አዲስ መገለጥ መሆኑን ሲያስረዳቸው ነው፡፡
2. ከማመናችን በፊት ያገባን ከሆነ ሰላመንን ብቻ ከትዳራችን ለመውጣት ማሰብ እንደማይኖርብን ያስተምረናል፡፡ ከዚህ ዓይነቱ ትዳር ለመውጣት ጳውሎስ የምንገደድበት አንድ ነገር ያላመነው ሰው አልፈልግም ብሎ ራሱ ሲወጣ ብቻ ነው፡፡
3. እነዚህ ሶስት ክፍሎች ሰዎች ከትዳራቸው መውጣት እንደሚኖርባቸው የሚያዙ ሳይሆኑ ሊወጡ የሚችሉበት ነጻነት እንዳላቸውና ምናልባትም ሌላ ማግባት የሚችሉበት መሰረት እንዳላቸው  የሚጠቁሙን ክፍሎች ናቸው፡፡ ይህንን ጥያቄ እኔ የምረዳው ያላመነው ሰው መለየት እየፈለገ ያላመነው ሰው ይድናል በማለት በጭንቀትና ሰላም በሌለበት ሁኔታ መቆየታቸው ለሰውየው ወይም ለሴትየዋ ደህንነትን እንደሚያመጣላቸው በምን እርግጠኛ ትሆናላችሁ የሚል መረዳት ነው ያለኝ፡፡
4. ይህ ክፍል የሚነግረኝ አንድ ነገር ሰዎች ሁሉ የወንጌል ጥሪ ሲደርሳቸው የሚገኙበት ሁኔታ አንድ አይነት እንዳልሆነና በተለያየ ሁኔታ ውስጥ እያለን እንደምንጠራ ነው፡፡ ይህ መመሪያ የሚሰራው ለቆሮንቶስ ቤ/ክ ብቻ ሳይሆን በማናቸውም አብያተ ክርስትያናት ውስጥ ለሚገኙ አማኞች ነው፡፡
5. በምሳሌነት የተጠቀመው መገረዝንና አለመገረዝን ነው፡፡ ምክንያቱም ለአይሁዳውያን ግርዛት የተስፋ ቃልን የሚያመለክት፣ የእግዚአብሄር ህዝብነትን ማረጋገጫ፣ የመታዘዝ ምልክትና የመሳሰሉትን ሁሉ ያካተተ ነገር በመሆኑ ዘሬ ተነስቶ ‹‹መገረዝ አይጠቅምም›› ሲባል ቀላል ሆኖ አይገኝም፡፡
6. የጳውሎስ ምክር መገረዝንና አለመገረዛቸውን እያሰቡ ለመንፈሳዊ ህይወት ምንም ፋይዳ በሌለው ነገር ጊዜያቸውን እንዳያጠፉና ዋነኛው ነገር ያም ለእግዚአብሄር በመታዘዝ ላይ እንዲያተኩሩ ነው የሚያስተምራቸው፡፡ ከዚህ ጥቅስ አንጻር የተገረዙትን ባልተገረዝኩ ብለው እንዳይጸጸቱና ያልተገረዙ ደግሞ ለመገረዝ ጥረት ማድረግ እንዳይጀምሩ ነው የሚያስተምራቸው፡፡
7. ሌላው በምሳሌነት የጠቀሰው ነገር ባርነትን ነው፡፡ ባሪያዎቹን የሚመክራቸው ያላችሁበት ሁኔታ አያስጨንቃችሁ በማለት ነበረ፡፡ ነጻ መውጣት መልካም ነገር ሲሆን እግዚአብሄርን መታዘዝ ግን ዋነኛ ነገር ስለሆነ ከዋነኛው ዓላማህ እንዳያዘናጋህ ትኩረትህን በእርሱ ላይ አታድርግ ለማለት ነው፡፡
8. ባሪያ ሆኖ የተጠራ ሰው በጌታ ነጻ ስለሆነና በህብረተሰቡ ውስጥ ጌታ የሆነ ሰው ደግሞ የጌታ ባሪያ በመሆናቸው ሁለቱም ቦታቸውን እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል፡፡

# ጥናት አስራ አራት 1ኛ ቆሮ 7፡25-40 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ደናግሉን የሚመከረው ሁሉም ባሉበት ሁኔታ በኖሩ እንደሚመርጥ ይናገራል፤ ይህንንም ስላለበት ምክንያት ሲናገር ችግሩ ምን እንደሆነ ባይናገርም ‹‹አሁን ካለው ችግር የተነሳ›› ይላል፡፡
2. በዚህ ዓለም ችግር አለባቸው የሚለው ያላገባ ሰው ረሃብ ቢኖር፣ ስደት ቢመጣ፣ ወይም በሽታ ሲከሰት ሚስቴና ልጆቼ የሚለው ሃሳብ ተጨማሪ መከራን ያመጣበታል ማለት ነው፡፡ ጳውሎስ ይህንን ዓይነት ነገሮችን ሲናገር በእኔ አስተያየት ሰዎች ቆም ብለው ሳያስቡ ሰው ስላደረገ ብቻ እንዳያደርጉ ለመርዳት እንጂ ስለትዳር መልካምነት ያለውን አመለካከት በኤፌሶን ምዕራፍ 5 ላይ ግልጽ አድርጎታል፡፡
3. የመጀመሪያው ምክንያት ዘመኑ አጭር ስለሆነና፤ ሁለተኛው ደግሞ የዚህ ዓለም መልክ ሃላፊ ስለሆነ ነው፡፡ የዘረዘራቸውን ሃሳቦች ያሰፈረበት ዋነኛው ምክንያት ትዳር፣ ሃዘን፣ ደስታና የመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ ጊዜያዊ መሆነቸውንና ከዘላለማዊው ነገር ሊያዘናጉን እንደማይገባ ለማስገንዘብ ነው፡፡
4. ያገባ ሰው ባሉን ወይም ሚስቱን ደስ ለማሰኘት የዚህን ዓለም ነገር ያስባል፤ ያላገባ ሰው ግን ጌታን ደስ ለማሰኘት ስለ ጌታ ነገር ያስባል፡፡ ማለትም ያገባ ሰው ልቡ ተከፍሏል፣ ያላገባ ግን አልተከፈለም፡ ጳውሎስ ይህንን ሲናገር በቁ35 ላይ እንደሚናገረው ልባቸው ሳይከፈል ለጌታ ለመኖር እንዲችሉ ነው፡፡
5. 1) በትዳር ውስጥ ያለሰው ሰውየው ወይም ሴትየዋ በህይወት እስካሉ ድረስ በገቡት ቃል ኪዳን የታሰሩ ናቸው፡፡ 2) ባሏ ከሞተ ማግባት ትችላለች፡፡ 3) የምታገባው ሰው አማኝ መሆን ይኖርበታል፡፡ 4) አማኝ እስከሆነ ድረስ የፈለገችውን ሰው የማግባት ነጻነት አላት፡፡
6. ሳታገባ መኖርን የመረጠላት ምክንያት የበለጠ ደስተኛ ልትሆን ትችላለች ብሎ ያመነ ስለሆነ ነው፡፡ ልንጠይቀው የሚገባን አንዱ ጥያቄ፣ ባገባ ነው ወይስ ባላገባ ነው የበለጠ ደስተኛ የምሆነው? የሚለው ነው፡፡
7. ለሰዎች ምርጫ የተተወ አንድ ነገር ብቻ ሲሆን ይኸውም ማግባት ወይም አለማግባት ነው(9)፣ ለሰዎች ምርጫ ያልተተው ደግሞ፡ ሰውነትን መከልከል(5)፣ ባልን ወይም ሚስትን መፍታት(39)፣ ሳያምን አብሮ መኖር የፈለገን መፍታት፣
8. የሚያስቡት ነገር የትዳር ጓደናቸውን ደስ ስለማሰኘት ነው፡፡ ትዳር ውስጥ የገባን ሰዎች የትዳር ጓደኞቻችን ደስ የሚሰኙበትን ነገር ለማወቅ መሞከርና እነርሱን ለማስደሰት ማሰብ እንደሚገባን እንማራለን ማለት ነው፡፡

# ጥናት አስራ አምስት 1ኛ ቆሮ 8፡1-13 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በነዚህ ሶስት ቁጥሮች ውስጥ በተለያየ መልኩ በብዛት የተጠቀሰው ‹‹እውቀት›› የሚለው ሃሳብ ሲሆን ይኸውም ሰባት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡
2. እውቀትን ያወዳደረው ከፍቅር ሲሆን፣ሐዋርያው በዚህ ክፍል ሊያስተላልፍ የፈለገው ዋነኛ ሃሳብ፤ እውቀት ያለፍቅር ለአማኝ የማይጠቅም ነገር ብቻ ሳይሆን የሚያስታብይ በመሆኑ ጎጂ ነገር ነው፡፡ እውቀት አያስፈልግም ማለቱ አይደለም፤ ምክንያቱም በ1ኛ ቆሮ 10፡1 12፡1 15፡34 ኣና በመሳሰሉት ክፍሎች እነዚህኑ ሰዎች ‹‹እንድታውቁ እፈልጋለሁ›› ሲላቸው እናነባለን፡፡
3. ‹‹ከእግዚአብሄር በቀር አምላክ ስለሌለ ጣዖት ሁሉ ከንቱ ነው፡፡›› እግዚአብሄር ከሌሎች አማልክት የሚለየው፡ ሁሉ ነገር ከእርሱ መሆኑና እኛም ደግሞ ለእርሱ መሆናችን ነው፡፡
4. ‹‹ይህን›› የተባለው በቁ4-6 ውስጥ የሰፈረው እውነት ሲሆን ሁሉም የተባሉት ደግሞ አማኞች ሁሉ የዚህ ዓይነቱ እውቀት የላቸውም ለማለት ነው፡፡
5. ይህ ቁጥር የሚናገረው ለጣዖት ስለተሰዋ ሥጋ ነው፡፡ አንዳንዶች ይህንን ሥጋ በመብላት የሚሰናከሉት ጣዖትን አስመልክቶ ተገቢ እውቀት ስለሌላቸው ነው፡፡ ምግብ በራሱ ለመንፈሳዊ ህይወት ምንም ዓይነት አስተዋጽዖ እንደሌለው ያሳየናል፡፡
6. ነጻነት እንዳላቸው የሚናገረው ጣዖትን አስመልክቶ ትክክለኛ እውቀት ያላቸውን ሲሆን፤ በዮሐ 8፡32 ኢየሱስ እውነትን ማወቅ አርነት እንደሚያወጣ የተናገረው በእነዚህ ሰዎች ህይወት እንደተፈጸመ እንረዳለን፡፡ በደካማነት የጠቀሳቸው ደግሞ የዚህ ዓይነቱ እውቀት የሌላቸውን ሰዎች ሲሆን እነዚህም ሰዎች ነጻ እንዲወጡ ካስፈለገ እውነት የሆነውን ቃል መማርና ማወቅ ያስፈልጋቸዋል፡፡
7. በነዚህ በሁለቱ መሃል የፍቅር ግንኙነት፤ ማለትም እውነቱን የተረዳው ወገን ላልተረዳው ወገን እንቅፋት እንዳይሆንበት የመጠንቀቅ ግዴታ አለበት፡፡ እውቀት አለኝ ብሎ ነጻነትን አለገደብ መጠቀም ቁ1 ላይ እውቀት ያስታብያል የሚለውን እውነት ግልጽ አድርጎ ያሳያል፡፡
8. ይህንን በማድረግ የምንበድለው ወንድማችንን ብቻ ሳይሆን ለእርሱ የሞተለትን ክርስቶስን ጭምር ነው፡፡ ጳውሎስ ይህንን አስመልክቶ የደረሰበት ውሳኔ ወንድሙ ከሚሰናከል የሚወደውን ሥጋ አለመብላት ነው፡፡

# ጥናት አስራ ስድስት 1ኛ ቆሮ 9፡1-15 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ነጻ ሰው አይደለሁምን? ሃዋርያ አይደለሁምን? ጌታን አላየሁትምን፣ እናንተስ የድካሜ ፍሬ አይደላችሁምን? የሚሉት ሲሆኑ፤ የሚጠይቃቸው መልሱን ሳያውቅ ቀርቶ ሳይሆን የአዎንታ መልስን በመጠበቅ ነው፡፡
2. የመብላትና የመጠጣት መብት የለንምን፣ አማኝ ሚስት ይዘን የመዞር መብት የለንምን? ጥረን ግረን መኖር ያለብን እኔና በርናባስ ብቻ ነንን? የሚሉት ናቸው፡፡ አንደኛው ልዩነት፤ በቁ1-2 ያሉት በማንነቱ ላይ ያተኮሩ ሲሆን በቁ4-5 ያሉት ደግሞ በአገልጋዮች መብት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ሁለቱም መልስ ከሰሚዎቹ የማይጠይቁ ዓይነቶች በመሆናቸው በዚህ ይመሳሰላሉ፡፡
3. ጥያቄዎቹ፡ በገዛ ገንዘቡ በወታደርነት ማገልገል አለወይ? ወይን የተከለ ፍሬውን አይበላም ወይ? ከብት የጠበቀ ወተቱን አይጠጣም ወይ የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ያላቸው ተመሳሳይነት ከሚደክሙበት መስክ ዋጋቸውን ወይም ደሞዛቸውን ያገኛሉ የሚል መልዕክት አለው፡፡
4. በቁ7 ላይ የሰፈሩት ጥያቄዎች በማናቸውም መስክ የለፋ ሰው ከለፋበት መስክ ምግቡን ወይም ደመወዙን ሊያገኝ እንደሚገባው ሲጠቁም፤ 8-10 ያሉት ቁጥሮች ደግሞ በሰው አመለካከት ነገሮች ስሜት የሚሰጡ ቢሆኑም እንኳን ሥልጣን የሚኖራቸው ግን በእግዚአብሄርም ቃል ሲደገፉ ብቻ እንደሆነ ያረጋግጥልናል፡፡
5. ‹‹…ትልቅ ነገር መሆኑ ነውን?›› በማለት መንፈሳዊው ነገር የሚበልጥ መሆኑን ይጠቁመናል፡፡ ጳውሎስ ይህችን ቤተ ክርስትያን የመሰረተና ለብዙዎቻቸውም በጌታ መወለድ ምክንያት የሆነ ስለሆነ መብቱን መጠየቅ ቢያስፈልግ ከሌሎቹ ይልቅ በእርሱ ያምራል፡፡ እርሱ ግን ለወንጌል እንቅፋት እንዳልሆን ይህንን መብቱን መጠቀም እንዳልፈለገ ይነግረናል፡፡
6. በቤተ መደቅደስ የሚያገለግሉና በመሰዊያው የሚያገለግሉትን ሰዎች ይጠቅሳል፡፡ እነዚህ ክፍሎች ሁለቱም ብሉይ ኪዳንን የሚወክሉ፤ ማለትብ በብሉይ የተነገሩ ሃሳቦች ናቸው፡፡
7. በዚህ ቁጥር ደግሞ ሐዋርያው የተጠቀመበት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ሃሳብ አስመልክቶ ትዕዛዝ እንደሰጠ ነው የሚናገረው፡፡ ለዚህም ማቴ 10፡10 ንና ሉቃ 10፡7ትን ተመልከት፡፡
8. 1) ማንኛውም ሰው ለለፋበት ክፍያ መከፈሉ ማንም ሰው የሚቀበለው ነገር ነው፡፡ ቁ7 2)በብሉይ ኪዳን እግዚአብሄር ደንግጎታል ቁ8-10 3)ጌታ ኢየሱስ አዟል፡፡ ቁ14 አገልጋዮች ራሳቸውን መጠየቅ የሚኖርባቸው ነገር፡ በቅዱሳን መሃል ሳገለግል እየዘራሁ ያለሁት መንፈሳዊ ነገር ነው ወይስ የተቀያየጠ? የሚገለገለው ህዝብ ደግሞ ጥያቄው ሊሆን የሚገባው፡ ይህ ሰው በመሃላችን መንፈሳዊ ነገርን ነው ወይ የሚዘራው? ከሆነስ ለሥጋው የሚያስፈልገውን አሟልተንለታል ወይ ብለው ሊጠይቁ ይገባል፡፡

## ጥናት አስራ ሰባት 1ኛ ቆሮ 9፡16-27(ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የዚህ ክፍል ዋና ትኩረት በወንጌል ስብከት ላይ ነው፡፡ ሃዋርያው ይህንን ሲል ወንጌልን ሰበክሁ ብዬ የምኩራራበት ወይም የምፎክርበት ነገር አይደለም፤ ምክንያቱም ወንጌልን የምሰብከው በራሴ አነሳሽነትና ራሴ የጀመርኩት ሃሳብ ሳይሆን ከራሱ ከእግዚአብሄር የተሰጠኝ አደራ ስለሆነ የተባልኩትን ማድረግ ግዴታዬ ስለሆነ መኩራሪያዬ ሊሆን አይችልም ማለቱ ነው፡፡
2. የተጣለበትን አደራ እንደ ግዴታ ሳይቆጥር ከልቡ በፈቃደኝነት በደስታ ማድረግ እንደሚችልና፤ በሌላ በኩል ደግሞ ግዴታው እንደሆነ ብቻ በማሰብ ሃላፊነቱን ለመወጣት ያህል ማድረግ እንደሚቻል ያሳየናል፡፡ ሽልማት የሚያስገኘው የመጀመሪያው መንገድ ሲሆን፤ ሽልማቱ አድርጎ የሚናገረውም ወንጌልን ያለክፍያ በመስበክ ወይም ከወንጌል ስብከት ሊቀበል የሚችለውን የክፍያ መብቱን ካለመጠቀም የሚገኘውን ውስጣዊ እርካታና የልብ ደስታ ማግኘት እንደሆነ ይናገራል፡፡
3. ነጻ ሰው እንደሆነና የማንም ሰው ባሪያ እንዳልሆነ ይነግራቸዋል፡፡ ለሰው ሁሉ ራሱን ባሪያ ለማድረግ ፈቃደኛ የሆነበት ምክንያት ብዙዎችን በወንጌል ወደ እግዚአብሄር መንግሥት ይመልስ ዘንድ ነው፡፡
4. በወንጌል ሊደርሳቸው ከሚሞክራቸው መሃል አራቱን የዘረዘረ ሲሆን፤ እነዚህም አይሁድ፣ ከህግ በታች ያሉ፣ ህግ የሌላቸውና ደካሞች በማለት ይዘረዝራቸዋል፡፡ ጥረቱ በነዚህ ላይ ብቻ እንደማያበቃ ከነዚህ ያለፈም አይነት ሰው ቢኖር ቁ22 እንደሚያጠቃልለው መረዳት ይቻላል፡፡
5. በብዛት የሰፈረው ሃሳብ ‹‹እመልስ ዘንድ›› የሚለው ሲሆን አምስት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል ከዚያም ጋራ ‹‹አድን ዘንድ›› የሚለው ተመሳሳይ የሆነ ሃሳብም በተጨማሪ እናያለን፡፡ ይህንን ለማድረግ የተነሳሳባቸው ሁለት ምክንያቶች፡ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለመመለስ ለማዳን(ቁ22) እና፣ በራሱ በኩል ደግሞ ከወንጌል በረከት ለመካፈል(ቁ23) የሚሉት ይሆናሉ፡፡
6. ጳውሎስ በቁ22 ላይ እንደምንመለከተው ሰዎች ሁሉ ይድናሉ የሚለውን ሃሳብ ይዞ የተነሳ እንዳልሆነና ማናቸውም ያህል ሰዎች ቢድኑ ይህንን መስዋዕትነት ለመክፈል ፈቃደኝነቱን ያሳየናል፤ ‹‹በሚቻለኝ ሁሉ አንዳንዶችን አድን ዘንድ›› ነው የሚለው፡፡ ይህ እኛም ወንጌልን ስንናገር የነገርናቸው ሰዎች ሁሉ ራሳቸውን ለክርስቶስ ይሰጣሉ የሚለውን ሃሳብ ከያዝን ወደ ተስፋ መቁረጥ ሊያመጣን ስለሚችል የጳውሎስን ፈለግ መከተል ብልህነት ይመስለኛል፡፡
7. ሯጮቹ በሁለቱም በኩል ብዙዎች ናቸው፤ ሽልማትን አስመልክቶ ግን በምድሩ አንዱ ብቻ ሲቀበል በሰማያዊው ግን ሽልማት እንደሚቀበል ሆነው የሮጡ በሙሉ አክሊሉን ይቀበላሉ፡፡ እነዚህ ሁለት ነገሮች በመጀመሪያ ደረጃ ራስን መግዛት የሚጠይቅ ሲሆን ሌላው ደግሞ በሙሉ ጉልበት በመስራት መድከምን ይጠይቃል፡፡
8. ግብ እንደሌለው ሰው በከንቱ አይሮጥም፣ ነፋስ እንደሚጎስም ሰው እንዲያው አይታገልም፣ ሰውነቱን እየጎሰመ እንዲገዛለት ያደርጋል፡፡ የሚመክረው አንድ ምክር ሽልማት እንደሚቀበል ሰው እንዲሮጡ ነው፡፡ ሽልማት እንደሚቀበል ሰው መሮጥ ሲባል፡ ብዙ ዝግጅትና ልምምድ፣ ኮተት ሳይሸከም፣ ትክክለኛ ትጥቅ የሚታጠቅ፣ የሚበላውንና የሚጠጣውን የሚመርጥ፣ በተሰመረለት መስመር ላይ ብቻ የሚሮጥና የመሳሰሉትን ሁሉ ያካትታል፡፡

# ጥናት አስራ ስምንት 1ኛ ቆሮ 10፡1-13 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እነዚህ አባቶች የተባሉት እግዚአብሄር ከግብጽ ምድር በተዓምራቱ ያወጣቸው ሁሉ ናቸው፡፡ እነርሱ የተለማመዷቸው፡ ሀ) ከደመና በታች መሆን ለ) በባር ውስጥ መሻገር ሐ) መንፈሳዊ ምግብ ሙብላት መ) መንፈሳዊ መንፈስ መጠጣት
2. ከሙሴ ጋራ ለመተባበር በደመናና በባህር መጠመቃቸው እኛ ከክርስቶስ ጋራ አንድ መሆናችንንና መተባቸራችንን በጥምቀት እንገልጻለን፤ እነርሱ መናን በሉ፣ እኛ ደግሞ የህይወት እንጀራ የሆነውን ክርስቶስን ተመግበናል፤ እነርሱ መንፈሳዊ ውሃ ጠጡ፣ እኛ ደግሞ ከህይወት ውሃ ጠጥተናል፡፡ ቁ4 እንደሚናገረው ያ ውሃ የፈለቀውና ዓለት በመባል የተነገረለት ክርስቶስ እንደነበረ እንረዳለን፡፡
3. በእነዚህ አባቶች እግዚአብሄር ደስ ስላልተሰኘ በበረሃ ወድቀው እንደቀሩ እናነባለን፡፡ በምድረበዳ የቀሩትን ቁጥር ‹‹ብዙዎች›› በማለት ይነግረናል፡፡ ይህንን ቁጥር ለማወቅ ካስፈለገ ከግብጽ የወጡትና ሃያ አመት የሆናቸው ሁሉ ማለትም ከኢያሱና ከካሌብ በስተቀር ማለት ነው ሁሉም ማለት ይቻላል፡፡
4. አምስቱ ሃጥያቶች፡ መመኘት፣ ጣዖት ማምለክ፣ ዝሙት፣ ጌታን መፈታተንና ማጉረምረም ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ ሃጥያት የወደቁትን ሰዎች ቁጥር ‹‹አንዳንዶቹ›› በማለት ነው የሚናገረው፡፡ የተለያዩ ሰዎች በተለያዩ ፈተናዎች መውደቅ የሚያስተምረኝ፡- የሰዎች ሁሉ ፈተና አንድ እንዳልሆነና ለአንዳንዶቻችን ከባድ ሆኖ የሚጥለን ፈተና ለሌሎቻችን የዚያን አይነት ክብደት እንደማይኖረው ማየት እንችላለን፡፡
5. ዝሙት የፈጸሙት፣ ጌታን የተፈታተኑትና፣ ያጉረመረሙት ሰዎች ቅጣታቸው ምን እንደነበረም እዚሁ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ይህ የሚያስተምረን ምንም እንኳን እግዚአብሄር ብዙ የባረከንና በህይወታችን ብዙ መልካም ነገሮችን ያለማመደንም ቢሆን፤ ፈተና በመጣ ቁጥር ከእግዚአብሄር ይልቅ ስጋችንን መታዘዝ ስንጀምር ይዘግይ እንጂ ቅጣት መኖሩ እንደማይቀር እንማራለን፡፡
6. በእኔ አመለካከት እዚህ የተዘረዘሩት አምስቱም ሃጥያቶች በዘመናችን በሰፊው የሚሰሩና ለብዙዎች እንቅፋት እንደሆኑ አያለሁ፡፡ መንፈስ ቅዱስ ይህንን ታሪክ ያሰፈረልንን ምክንያት በግልጽ ነግሮናል፤ ይኸውም እኛን ለማስጠንቀቅ ተጻፈ፡፡
7. ‹‹እኛ›› ሲል የሚጠቀልለው አማኝን በሙሉ ነው፡፡ ከፍሉ ትኩረቱን ያጠበበው ተደላድያለሁ፣ ምንም ልሆን አልችልም ብሎ ለሚሉ ዓይነት አማኞች ነው፡፡ በተለይም እንደ ሙሴና አሮንን የመሰሉ ሰዎችን ወደ ከነዓን እንዳይገቡ ካደረገ እኛም በክርስቶስ አምነን ብንድንም፤ እግዚአብሄር ያሰበልንን የድልና የደስታ ህይወት ማለትም መጽሃፍ ቅዱስ ህይወት እንዲበዛላችሁ የሚለውን ዓይነት ህይወት ለመያዝ በጥንቃቄ መኖርን ያበረታታናል፡፡
8. መጠንቀቅ የሚኖርብን ነገሮች፡ ክፉ ከመመኘት፣ ጣዖት ከማምለክ፣ ዝሙት ከመፈጸም፣ ጌታን ከመፈታተንና፣ ከማጉረምረም መጠበቅ ያስፈልገናል፡፡ የጌታን ታማኝነት መረዳት በመጀመሪያ ደረጃ እርሱ ሳያውቀው የሚመጣብኝ ነገር እንደሌለና ስለዚህም ከአቅሜ በላይ የሆነውን ነገር እንዲመጣብኝ ስለማይፈቅድ በተስፋ መቋቋም እችላለሁ፡፡

# ጥናት አስራ ዘጠኝ 1ኛ ቆሮ 10፡14-11፡1(ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ቁጥር ላይ የታዘዙት ከጣዖት አምልኮ እንዲሸሹ ነው፡፡ አራቱ እንድንሸሽ የተነገሩን ነገሮች፡ ከጣዖት አምልኮ፣ ከዝሙት፣ ከክፉ ምኞትና ከገንዘብ ፍቅር ናቸው፡፡
2. ይህ ምግብ እንደሚበላበት ቦታ አድርጎ የሚናገረው አማኞች በሚሰበሰቡበት ወይም በእኛ አጠራር ቤተ ክርስትያን በምንለው ስፍራ ነው፡፡ በነዚህ ቁጥሮች የተናገረውን በአንድ አረፍተ ነገር ለማጠቃለል፡ ‹‹ለአጋንንት የተሰዋን ሥጋ፤ ለጌታ እራት አድርጎ ማቅረብ የማይገባ ነገር ነው፡፡››
3. የመጀመሪያው አንድ ነገር የተፈቀደ እንኳን ቢሆን፤ ለሌሎች ወይም ለራሳችን እድገት እስካልጠቀመ ድረስ ማድረግ አይኖርብንም፣ ሌላኛው ደግሞ የተፈቀደው ነገር የእኛን ህይወት ወይም የሌሎች እስካላነጸ ድረስ ስለተፈቀደ ብቻ ማድረግ አይገባንም፡፡ ከዚህም ጋራ ለእኛ ጥቅም ቢኖረውም እንኳን ሁልጊዜ በራሳችን ላይ ብቻ ከማተኮር መቆጠብም እንደሚኖርብን በተጨማሪ ይመክረናል፡፡
4. ይህ ክፍል ደግሞ በገበያ ሥፍራ ባለው ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ ምክሩም ሳንጠራጠር ሁሉን መብላት እንደምንችል ነው፡፡
5. ያላመነ ሰው ቤት ስንጋበዝ በሚሆነው ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በገበያ ሥፍራ ከሚሆነው ምክሩ ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም የተገኘውን ሳይጠራጠሩ እንዲበሉ ነው የተነገራቸው፤ ሁለቱን የሚለያቸው ‹‹ነገር ግን›› በማለት ሰውየው ስጋው ከየት እንደመጣ ከነገረህ አትብላ የሚል ትልቅ ሃላፊነትን ጨምሮበታል፡፡
6. በቁ31 ላይ የሰጠው መመሪያ ህይወታችንን ሁሉ በእርግጠኛነት ልንመራ የምንችልበት ትልቅ እውነት ነው እላለሁ፡፡ ይህንን መመሪያ ከመከተል ሊገኙ የሚችሉትን ጥቅሞች እያንዳንዱ የጥናት ተካፋይ ሃሳቡን እንዲሰነዝር ጊዜ ይሰጠው፡፡
7. ሰውን ሁሉ ለማስደሰት እጥራለሁ ሲል ቀደም ሲል በ1ኛ ቆሮ 9፡19-23 ባለው ክፍል እንደተናገረው ሰዎቹ በሚገኙበት ሁኔታ ውስጥ ራሴን በማስገባት ልባቸውን ለወንጌል መልካም እርሻ እንዲሆን አዘጋጀዋለሁ ማለቱ እንጂ ወንጌልን እንደሚስማማቸው አድርጌ አቀርብላቸዋለሁ ማለቱ አይደለም፤ ለዚህም መረጃ የሚሆነን 1ኛ ተሰ 2፡4ትንና ገላ 1፡10ርን ማንበብ ሃሳቡን ግልጽ ያደርግልናል፡፡ ደስ ከተሰኙትም ሰዎች መካከል እንኳን ብሆን ሁሉም ደህንነትን ያገኛሉ የሚል አስተሳሰብ እንደሌለውና፤ ነገር ግን የሚቻለውን ያህል ብዛት ያላቸው ሰዎች እንዲድኑ ጥረቱን አያቆምም ማለት ነው፡፡
8. 1ኛ ቆሮ 9፡22-23 ትንና 1ኛ ቆሮ 11፡32-33ት በአንድነት ሲነበቡ ሰውን ሁሉ ማስደሰት እና እንቅፋት አለመሆን የሚሉት ሃሳቦች ከተለያዩ አይነት ሰዎች ጋራ አንድ መንገድ ብቻ ይዞ በዚያ ድርቅ ማለት እንዳልሆነ፤ ነገር ግን እንደ እያንዳንዱ ማንነት ወንገልን ለማቅረብ የምቻልበት መንገድ ሊኖር እንደሚችል ነው ሃዋርያው የሚያስተምረን፤ ይህ ካልሆነ ግን ለወንጌል እንቅፋት መሆን እንደሚቻል ያስገነዝበናል፡፡ ኦርቶዶክስ ጓደኛ ያለው ሰው ያንን ሰው በወንጌል መድረስ ከፈለገ ጾሙን አብሮ መጾም ይችላል፡፡

# ጥናት ሃያ 1ኛ ቆሮ 11፡2-16 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የሚያመሰግንባቸው አንደኛው ምክንያት በሁሉ ነገር ስለሚያስቡለትና ሁለተኛው ደግሞ ከእርሱ የተማሩትን ትምህርት አጥብቀው ስለያዙ ነው፡፡ በአንዱ ቦታ ምስጋና በሌላው ደግሞ አላመሰግናችሁም ማለቱ የሚያስተምረን፤ ሰዎችን በጥፋታቸው ጊዜ ብቻ መውቀስ ሳይሆን መመስገን በሚያስፈልጋቸውም ጊዜ ማመስገንን እንድንማር ይረዳናል፡፡
2. እንዲያውቁ የፈለጋቸው ነገሮች፡ 1) የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ እንደሆነ 2) የሴት ራስ ወንድ እንደሆነ 3) የክርስቶስ ራስ እግዚአብሄር እንደሆነ የሚሉት እውነቶች ናቸው፡፡ ብዙ ጊዜ አከራካሪ ሆኖ የሚገኘው መካከለኛው ማለትም የሴት ራስ ወንድ ነው የሚለው ነው፤ ለዚህም ምክንያት ሊሆን የሚችለው በዘመኑ የተነሱት የሴቶችን መብት አስከባሪና በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ማለት ሴት ከወንድ የበላይ ነው ሁለቱ እኩል አይደሉም የሚለው የተሳሳተ አመለካከት ይመስለኛል፡፡
3. ወንድ ራሱን የሚያዋርደው ራሱን ተከናንቦ ሲጸልይ ሲሆን፤ ሴት ደግሞ ራሷን ሳትሸፍን ስትጸልይ ራሷን ታዋርዳለች፡፡
4. ወንድ የእግዚአብሄር ምሳሌና ክብር ስለሆነ ነው፡፡ ሴት ደግሞ የወንድ ክብር እንደሆነች ይነግረናል፡፡
5. ሴት ከወንድ ተገኘች የሚለው በዘፍ 2፡21-22 እና በ1ኛ ጢሞ 2፡13 ማየት ሲቻል፤ ሴት ለወንድ ተፈጠረች የሚለው ደግሞ በዘፍ 2፡18 ማየት ይቻላል፡፡ እነዚህን ሃሳቦች የተጠቀመው ሴት በስልጣን ስር መሆንዋን የሚያሳይ ምልክት በራስዋ ላይ እንድታደርግ የሚለውን እውነት ለማስተማር ነው፡፡
6. በቁ11-12 ላይ ሴት ያለወንድ ወንድም ያለሴት አይሆንም ሲል ሴት ከወንድ ትገኝ አንጂ ሴት ካልወለደችው ሌላ ወንድ ሊገኝ የሚችልበት መንገድ የለም በሚል ሃሳብ ከላይ ለተናገረው ሃሳብ ሚዛን ይሰጠዋል፡፡ ‹‹በጌታ ዘንድ›› ሲል ይህንን እውነት የራሳቸው አድርገው እንዲኖሩ የሚጠበቅባቸው አማኞች ሲሆኑ፤ ‹‹የሁሉም መገኛ እግዚአብሄር ነው›› የሚለው ደግሞ ማንም የበላይነት ስሜት ውስጥ እንዳይገባ ሁላችንም ምንጭ እንዳለንና ያ ምንጭም እግዚአብሄር እንደሆነ ያስገነዝበናል፡፡
7. ፈራጅ አድርጎ የሚያቀርበው ራሳቸውን አንባቢዎቹን ነው፡፡ ጥያቄ ሆኖ የቀረበው ነገር ‹‹ሴት ራሷን ሳትሸፍን ወደ እግዚአብሄር መጸለይ ይገባታልን?›› የሚለው ነው፡፡ እንዲፈርዱ የተጠየቁትም ተፈጥሮን አስመልክቶ ነው፡፡
8. ለቆሮንቶስ አማኞች ብቻ እንዳልሆነ ቁ16 ይህንን ግልጽ አድርጎ አስፍሮልናል፡፡ በዚሁ ቁጥር ላይ እንደ ጳውሎስ አነጋገር ክርክርን ማንሳት ሳይሆን ሃላፊነቱ ከቃሉ ለተረዳሁት ነገር መታዘዝ እንደሆነ ይጠቁመኛል፡፡

# ጥናት ሃያ አንድ 1ኛ ቆሮ 11፡17-34 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ስብሰባቸው ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝን ይናገራል፡፡ ዋነኛ አድርጎ ያየው ችግር በመሃላቸው ያለውን የመከፋፈል መንፈስ ነው፡፡
2. ምንም እንኳን መለያየት በጎ ነገር እንዳልሆነ ቢታወቅም፤ ከእግዚአብሄር መልካም ካልሆነው ነገር መልካምን ነገር ማለትም የእርሱን እውነት የሚከተለውንና በራሱ መንገድ የሚሄደውን መለያ አድርጎ ተጠቅሞበታል፡፡ በዚህ ቁጥርና በ1ኛ ቆሮ 10፡5 መሃል የማየው ተመሳሳይነት፡ በሁለቱም ውስጥ እግዚአብሄርን በመታዘዝ የሚኖሩና ሌሎች ደግሞ በሚያውቁት እውነት የማይኖሩ ሰዎች መኖራቸውን ስናይ፤ በሁለቱም ሥፍራዎች ያልታዘዙት ፍርድ እንደደረሰባቸው በግልጽ ይታያል፡፡
3. እነዚህ ሰዎች የሚበሉት የጌታ ራት ተብሎ ሊጠራ እንደማይችል ነው የሚናገረው፤ ለዚህም የሚሰጣቸው ሁለት ምክንያቶች፡ የመጀመሪያው ራቱን ሲበሉ አለመጠባበቃቸውና፤ ሁለተኛው ደግሞ አንዱ ሲራብ ሌላው እስኪሰክር መጠጣት ነው፡፡
4. 1) የምትበሉበትና የምትጠጡበት ቤት የላችሁምን? 2) የእግዚአብሄርን ቤተ ክርስትያን በመናቅ፤ ምንም የሌላቸውን ታሳፍራላችሁን? 3) በዚህ ነገር ላመስግናችሁን? የሚሉት ናቸው፡፡ ሲበሉ አለመጠባበቃቸውንና አንዳንዶቹ ሲራቡ ሌሎች እስኪሰክሩ መጠጣታቸውን የእግዚአብሄርን ቤ/ክ እንደመናቅ ሆኖ ቀርቧል፡፡
5. የጌታ ራት ምንጩ ከራሱ ከጌታ እንደሆነ፣ የሥጋው መቆረስና የደሙ መፍሰስ ለእኛ እንደሆነ፣ የተሰጠንም በመታሰቢያነት እንዲያገለግለን ነው፡፡ ከእኛ የሚጠበቀው አንድ ነገር ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን መናገር ነው፡፡
6. ለመብላትና ለመጠጣት ከመቅረቡ በፊት ራሱን ሊመረምር ይገባል፡፡ ምክንያቱም ሳይገባው የበላና የጠጣ በራሱ ላይ ፍርድን ያመጣልና ነው፡፡
7. ብዙዎች ደክመዋል፣ ብዙዎችም ታመዋል፣ አንዳንዶች ደግሞ አንቀላፍተዋል (ሞተዋል) ይላል፡፡ ለፍርድ ምክንያት ሆኖ የቀረበው ነገር ራስን አለመመርመር ነው፡፡ ጌታ የሚገስጻን ከዓለም ጋራ እንዳንኮነን ሲሆን፤ ይህ ስለጌታ የሚያሳየኝ ተግሳጹ (ቢገድልም እንኳን) ፍቅር የተሞላበት እንደሆነ ነው፡፡
8. የጳውሎስ ምክር በመጨረሻ ላይ፤ የጌታን ራት ለመብላት ሲሰባሰቡ እርስ በእርስ እንዲጠባበቁና፤ የተራበ ሰው ካለ አስቀድሞ ቤቱ በልቶ እንዲመጣ ነው፡፡ ለዚህ አይነት ሰው ምክሬ የሚሆነው፤ በውስጥህ የምታውቀው ሃጥያት ካለ ተናዘዝ፣ ከሰው ጋራ ማስተካከል ያለብህ ነገር ካለ አስተካክል፤ ከዚያ በተረፈ ሥጋው የተቆረሰውና ደሙ የፈሰሰው እንዳንተ ላሉ ሃጥያተኞች ስለሆነ፤ ሃጥያተኛ መሆንህ ከዚህ በረከት ሊያርቅህ ሳይሆን ሊያቀርብህና በሙሉ ልብ ልትካፈለው ይገባል እላለሁ፡፡

# ጥናት ሃያ ሁለት 1ኛ ቆሮ 12፡1-11 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ጳውሎስ እንዲያውቁ የሚፈልገው ነገር ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ነው፡፡ ወደ ጌታ ዘወር ከማለታቸው በፊት ዲዳ ወደሆኑ ጣዖታት ወዲያና ወዲህ ሲወሰዱ እንደነበረ ነው የሚያስታውሳቸው፡፡
2. ሁለቱ ያሰፈራቸው መንፈሳዊ እውነቶች፡ የመጀመሪያው ማንም በእግዚአብሄር መንፈስ ሆኖ ሲናገር ‹‹ኢየሱስ የተረገመ ነው›› ሊል እንደማይችልና፤ ሁለተኛው ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር ‹‹ኢየሱስ ጌታ ነው›› ማለት እንደማይችል ነው፡፡ ማናቸውም ሰው እነኚህን ሁለት አይቻሉም የተባሉትን ነገር ከአፉ ማውጣት አይችልም ማለት ሳይሆን፤ ከልቡ ሆኖ ከእምነት በመነጨ አነጋገር እነዚህን ነገሮች መናገር አይቻልም ማለቱ ነው፡፡
3. እነዚህ ሶስት ርዕሶች፡ ስጦታዎች፣ አገልግሎትና፣ አሰራር የሚሉት ናቸው፡፡ አንድ የሚያደርጋቸው ነገር፤ ሁሉም ‹‹ልዩ ልዩ›› ናቸው በሚል ቃል ነው የታሰሩት፡፡
4. መንፈስ ቅዱስ እንደ ስጦታ አዳይ፣ ጌታ የሱስ በአገልግሎቶቹ እንደተገልጋይና እግዚአብሄር አብ ደግሞ በማናቸውም በሚሰሩት የአገልግሎት አይነቶች ሁሉ ውስጥ ሥራውን በአማኞች ውስጥ እንደሚሰራ ሆኖ ነው የቀረበው፡፡ ከዚህ መማር የምችለው በምድር በምናገለግለው አገልግሎትና በሥጦታዎች የሥላሴዎች ሁሉ እጅና በረከት እንዲሁም ተሳትፎ እንዳለበት ነው፡፡
5. እነዚህ ሥጦታዎች የሚሰጡትም ለእያንዳንዱ አማኝ መሆኑን ክፍሉ ያረጋግጥልናል፡፡ ስጦታዎች ወይም መንፈስ ቅዱስን መግለጥ የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው፡፡
6. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተዘረዘሩትን ሁሉ ስንመለከት ግልጽ ሆኖ የሚታየው አንድ እውነት ቢኖር አማኝ ሁሉ ስጦታ ቢኖረውም ስጦታችን ግን የሁላችንም አንድ አይነት እንዳልሆነና ልዩ ልዩ መሆኑን ነው፡፡
7. በዚህ ቁጥር ላይ የሥጦታዎቹ ሁሉ ባለቤት መንፈስ ቅዱስ ራሱ እንደሆነ እናነባለን፡፡ ስለ ሥጦታ መናገር የምንችለው፤ ሥጦታ የተሰጠን ምንም ነገር ቢሆን በምስጋና እንቀበላለን፣ አክብረን እንይዘዋለን…ወዘተ፡፡
8. ራሱ ማለትም መንፈስ ቅዱስ እንደ ፈቀደ ያከፋፍላል ይላል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ስጦታውን ሲሰጥ ለቤተ ክርስትያን ማለትም ለጋራ ጥቅም ነው፡፡

# ጥናት ሃያ ሶስት 1ኛ ቆሮ 12፡12-21 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ክርስቶስን የሚያመሳስለው ከአካል ጋራ ነው፡፡ አነዚህ ሁለት እውነቶች፤ የመጀመሪያው ብዙ ብልቶች አንድ አካል የሚለውና ሌላው ደግሞ የመጀመሪያውን በማዟዟር አንድ አካል ብዙ ብዙ ብልት የሚለው ነው፡፡
2. ሁለቱ የተካሄዱት ነገሮች፤ በመንፈስ መጠመቅና፣ መንፈሱን መጠጣት የሚሉት ናቸው፡፡ በአንድ መንፈስ የተጠመቅነው እኛ ሁላችን አንድ አካል እንድንሆን ነው ይላል፡፡
3. በቁ12 ላይ ክርስቶስም እንደ አካል አንድ እንደሆነና ነገር ግን አካል አንድ ብልት ብቻ ሳይሆን ብዙ ብልቶች እንዳሉት የሚናገረው ሃሳብ፤ በቁ13ት ደግሞ አማኞች በምን መንገድ ወደዚህ ወደ ክርስቶስ አካል ውስጥ እንደሚገቡና ይህም ሥራ በማን እንደሚሰራ የሚያስተምረን ቁጥር ነው፡፡ ወደዚህ አካል የሚቀላቀሉትን ሰዎች ማንነት ሲናገርም፤ አይሁድ፣ የግሪክ ሰዎች፣ ባሪያና፣ ነጻ የሆኑ ሰዎችን ሁሉ የሚጨምር ሲሆን ሁሉን የሚጠቀልል ነገር መሆኑንም እኛ ሁላችን ብሎ የደመድመዋል፡፡
4. ሁኔታውን መካድ ያለውን እውነታ አይቀይረውም፡፡ ‹‹እኔ እጅ ስላልሆንኩ…›› ‹‹እኔ ዓይን ስላልሆንኩ…›› የሚሉት አነጋገሮች ሌሎችን ለመሆን የምናሳየውን ፍላጎት ይጠቁመናል፡፡
5. አንደኛው ሃቅ፤ ሰውነት ሁሉ አንድ ብልት ብቻ ቢሆን ሌሎቹ ብልቶቻችን የሚሰሯቸው ነገሮች ሁሉ ሊሰራቸው የሚችል እንደሌለ ሲያስገነዝበን፤ ሁለተኛው ደግሞ አዋቂው እግዚአብሄር እያንዳንዳችንን በትክክለኛ ቦታችን ስለመደበን ነው ይላል፡፡
6. የሃዋርያው ጥያቄ፤ ሁሉም አንድ ብልት ቢሆን ኖሮ አካል ከየት ይገኝ ነበር? ሃሳቡን የጠቀለለበት ዓረፍተ ነገር ‹‹ብልቶች ብዙ ናቸው፤ አካል ግን አንድ ነው፡፡›› የሚል ነው፡፡
7. በቁ15-20 የተመለከትናቸው ቁጥሮች ያተኮሩበት ችግር አማኞች ለእነርሱ እግዚአብሄር ከሰጣቸው ሥፍራ ይልቅ የሌሎችን የመመኘትና በሆኑት ነገር አለመርካትን የሚያሳይ ወይም (ራስን ታች ሌሎችን ላይ) አድርጎ ማየት ሲሆን፤ ይህ በቁ21-22 ያለው ክፍ ደግሞ እነርሱ የበላይ ሆነው የሌሎችን ቦታ ዝቅ አድርጎ የማየትን ወይም (ራስን ላይ ሌሎችን ታች) አድርጎ የማየት ችግር ነው፡፡ በዘመናችን ሁለቱም በብዛት በአማኞች መሃል የሚገለጡ አሳዛኝ እውነታዎች ናቸው፡፡
8. ይህንን ቁጥር በትክክል መረዳት ለሁለቱ ችግሮች መፍትሄ ሊሆን የሚችለው፤ በመጀመሪያ ‹‹እግዚአብሄር እንደ ወደደ›› የሚለው የእርሱን ፈቃድ መፈጸም የሁሉ አማኝ ፍላጎት ሊሆን ስለሚገባ፤ ሌላው ደግሞ ‹‹በየቦታው መድቧል›› ሲል በዘፈቀደ የተደረገ ነገር ሳይሆን በመለኮታዊ ጥበብ ለቦታው ያስፈልጋል የሚለውን በትክክል አስቦበት ያደረገው መሆኑን ስለሚያሳየን የዝቅተኛነት ስሜትም ሆነ የትዕቢት ስሜት ሥፍራ ሊኖረው እንደማይገባ እንረዳለን፡፡

# ጥናት ሃያ አራት 1ኛ ቆሮ 12፡22-31 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ይህ ሃሳብ የተሰነዘረው በቁ21 ላይ የሰፈረውን የአታስፈልገኝም አመለካከት ለመጻረር ነው፡፡ ጳውሎስ በዚህ ክፍል የሚነግረን ደካማ የሚመስሉት የአካል ብልቶች እጅግ አስፈላጊ እንደሆኑ ነው፡፡
2. ደካማ የሚመስሉ፣ የተናቁ የሚመስሉ፣ የምናፍርባቸውና የማናፍርባቸው በማለት ተጠቅሰዋል፡፡ ከዚህ አነጋገሩ የምንማረው እውነት፤ እነዚህ ብልቶች ደካማ ይምሰሉ እንጂ ደካሞች እንዳልሆኑ፣ የተናቁ ይምሰሉ እንጂ የተናቁ እንዳልሆኑ ነው፡፡
3. ክብርና እንክብካቤ የሚገባው ለተናቁና ለምናፍርባቸው ብልቶቻችን ነው ይላል፡፡ ያገጣጠመው እግዚአብሄር ራሱ ሲሆን፤ አገጣጥሟል ሲልም እያንዳንዱ ብልት ለብቻው እንደ ደሴት ለብቻው የተቀመጠ ብቸኛ ነገር ሳይሆን ከሌሎች ሁሉ ብልቶች ጋራ የተያያዘና የተገጣጠመ መሆኑን ለማስረዳት ነው፡፡
4. አንደኛው መለያየት እንዳይኖርና፣ ሁለተኛው ደግሞ እርስ በእርሳቸው እኩል እንዲተሳሰቡ ነው፡፡ አለመለያየትና መተሳሰብ በብልቶች መሃል ሲኖሩ የሚከሰቱት ሁለት ነገሮች፤ የአንዱ ብልት ሥቃይ የሌላውም ብልት ሥቃይ መኖንና የአንዱ ብልት ደስታ የሌሎችም ሁሉ ደስታ ይሆናል ነው የሚለን፡፡
5. ሐዋርያት፣ ነብያት፣ መምህራን…ወዘተ፡፡ ቁ14 አካል ከብዙ ብልቶች እንደሚሰራ ያስተማረን ሲሆን፤ ይህ ቁጥር ደግሞ እኛ ሁላችን የክርስቶስ አካል ብንሆንም እያንዳንዳችን የተለያየ ብልቶች ማትም ልዩ ልዩ ስጦታ ተቀብለን በዚያ አካሉን እንደምናገለግል ያሳየናል፡፡
6. በእነዚህ ቁጥሮች ላይ እንደሚታየው ስጦታዎችን በማደላደልና በመስጠት እግዚአብሄር ብቻ የሚያደርገው ነገር እንጂ በሰው ፍላጎት ላይ የተመሰረተ እንዳልሆነ ግልጽ ያደርግልናል፡፡ በቁ31 ላይ የምናነበው ሃሳብ ሰጪውና አደላዳዩ እግዚአብሄር ራሱ ይሁን እንጂ፤ ሰዎች በብርቱ ሊፈልጉና ሊጸልዩ እንደሚችሉ ይጠቁመናል፡፡
7. ሁሉ ሐዋርያት ናቸውን? ሁሉ ነብያት ናቸውን? ሁሉስ መምህራን ናቸውን?…ወዘተ፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች የተጠየቁበት ምክንያት ከላይ ያስረዳቸውን እያንዳንዳችን ብልቶች እንደሆንና እያንዳንዳችንም የተለያየ ሃላፊነት እንደተሰጠን ለማረጋገጥ የተጠቀመበት ነው፡፡ የሚጠብቀው መልስም አይደለም የሚል ነው፡፡
8. በዚች ምድር ላይ እግዚአብሄር የሰጠንን ሃላፊነት ለመወጣት እንደሚገባ ለመወጣት ካስፈለገ፤ እኔ ለሌሎች የጌታ ልጆች ሁሉ አስፈልጋቸዋለሁ፤ እነርሱም ደግሞ ለእኔ ያስፈልጉኛል የሚል አማኝ ጤናማ የሆነ አመለካከት አለው ብዬ አምናለሁ፡፡

# ጥናት ሃያ አምስት 1ኛ ቆሮ 13፡1-13 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በሚጮህ ናስና በሚንሻሻ ጸናጽል ይመስለዋል፡፡ መላዕክትን በዚህ ሥፍራ መጠቀም የፈለገበት ምክንያት ጉዳዩ ልሳኑን ከመናገር ያለፈና የፍቅርን አስፈላጊነት ለማጉላት ሲል ያመጣው ነው፡፡
2. ልሳን፣ ትንቢት፣ እውቀትን መናገር (ቁ8)፣ እምነት (ቁ9)፣ የመስጠት ስጦታዎች (ሮሜ 12፡8) ይገኙበታል፡፡ ይህ ሃረግ ሶስት ጊዜ ተጠቅሶ ይገናል፡፡
3. ከነዚህ ሃረጎች ቀድመው የሚገኙት ሶስት ቃላት፡ ብናገር፣ ቢኖረኝና፣ ብዳርግ (ብሰጥ) የሚሉት ናቸው፡፡ አዎን እስማማለሁ፤ ምክንያቱም ስጦታዎች ወይ በአንደበት መናገርን፣ ወይ በጎ ነገር የማድረግንና ወይም ደግሞ በእምነት የተለያዩ ድንቅና ተዓምራትን በማድረግ ላይ የተመሰረቱ ናቸው ብዬ ስለማምንና ከነዚህ የወጣ በእኔ አመለካከት ስላላየሁ ነው፡፡
4. ከክፍሉ ውስጥ በማንበብ መዘርዘር ይቻላል፡፡ ይህንን ያደረገበት ምክንያት እኔ እንደሚመስለኝ ፍቅር አለኝ በማለት ለሚያስብና ለሚናገር ሰው ፍቅር ምን እንደሚመስል በማሳየት ሰውየው ራሱንን የሚለካበት ወይም የሚመለከትበት መነጽር ለማስቀመጥ እንደሚሆን አስባሁ፡፡
5. የቆሮንቶስ ቤተ ክርስትያን ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ይልቅ በስጦታዎች የበለጠገች ነች እላለሁ፤ ምክንያቱም 1ኛ ቆሮ 1፡11፣ 5፡2፣ 6፡7-8 እና የመሳሰሉትን ክፍሎች ስንመለከት እነዚህ ሰዎች ጳውሎስ ፍቅር ብሎ በሚጠራው ዓይነት እንደማይኖሩ ተገልጦ ይታያል፡፡ ፍቅር በክርስትና ማዕከላዊ ነገር ሆኖ ሊታይ የሚገባው፤ ያለፍቅር አገልግሎታችን ወይም የተሰጡን ሥጦታዎች ሁሉ ከንቱ ስለሚሆኑና ሌላው ደግሞ ህግጋት ሁሉ የሚጠቃለሉበት በፍቅር በመሆኑ ነው፡፡
6. በነዚህ ቁጥሮች ላይ ፍቅርን የሚያወዳድረው፤ ከእውቀት፣ ከልሳንና፣ ከትንቢት ጋራ ነው፡፡ እውቀት የሚሻርበት ምክንያት፤ አሁን ሊኖረን የሚችለው የእውቀት መጠን የተከፈለ ወይም ያልተሟላ ስለሆነ ነው ይለናል፤
7. ‹‹ልጅ›› የሚለው ቃል ሲሆን፤ በአንድ ቁጥር ውስጥ አምስት ጊዜ ተጠቅሶ እናገኘዋለን፡፡ ጊዜን የሚጠቁሙት ሁለት ቃላት ‹‹አሁን›› የሚለውና ››በዚያን ጊዜ›› የሚሉት ናቸው፡፡
8. ‹‹ ልጅ›› የሚለው ቃል የአሁኑን ያለንበትን ሁኔታ የሚወክል ሲሆን፣ ‹‹ጎልማሳነት›› የሚለው ደግሞ የሚመጣውን ዘመን የሚወክል ሃሳብ ነው፡፡ ቁጥር 13 ለምዕራፉ ሁሉ ጥሩ ማጠቃለያ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡
9. እነዚህ ስጦታዎች አይጠቅሙም ማለቱ አይደለም፤ በዚህ ክፍል ሊያስተላልፍ የፈለገው ዋነኛ ሃሳብ፤ ማናቸውም አይነት የጸጋ ስጦታ የመንፈስ ፍሬ የሆነው ፍቅር ካልታከለበት ከንቱ እንደሆነ ለማስገንዘብ ነው፡፡

# ጥናት ሃያ ስድስት 1ኛ ቆሮ 14፡1-12 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ቁጥር ላይ የተሰጡን ሁለት ትዕዛዞች፡ የመጀመሪያው ፍቅርን እንድንከታተልና፤ ሁለተኛው ደግሞ መንፈሳዊ ስጦታዎችን በብርቱ እንድንፈልግ ነው፡፡ አጥብቀን እንድንፈልገው የተነገረን ስጦታ፤ የትንቢት ስጦታ ነው፡፡
2. በነዚህ ቁጥሮች ላይ በልሳን መናገርንና ትንቢት የመናገርን ስጦታዎች ነው እያነጻጸረ የተናገረው፡፡
3. ልሳንን አስመልክቶ፡ በልሳን የሚናገር ሰው የሚናገረው ለእግዚአብሄር እንጂ ለሰው አይናገርም፣ የሚናገረው ምስጢርን ነው፣ የሚናገረው በመንፈስ ነው፣ የሚናገረውን የሚረዳ ከእግዚአብሄር በቀር የለም፡፡ ትንቢት መናገር የሚለው ሃሳብ የሚያጠቃልላቸው ሃሳቦች፡ ማነጽ፣ ማበረታታትና ማጽናናት የሚሉትን ያጠቃልላል፡፡ ትንቢት በአብዛኛው ወደፊት የሚሆነውን የመናገር ችሎታ እንደሆነ ነው የሚታሰበው፤ ይህ ግን ትንቢት የሚለው ሰፋ ያለ ትርጉም እንደሚኖረው ይጠቁመናል፡፡
4. ከዚህ ከፍል አነጋገር እነዚህን ሁለት ስጦታዎች የሚለያቸው ነገር የሚታነጸው ሰው ማንነት ማለትም፤ ራስን ማነጽና ቤተ ክርስትያንን ማነጽ ናቸው፡፡ ከዚህ ልንገነዘብ የምንችለው ነገር፤ አጥብቀን ልንፈልግ የሚገባን የስጦታ አይነት ቤተ ክርስትያንን የሚያንጹ ሥጦታዎችን እንደሆነ ነው፡፡
5. በመጀመሪያ ደረጃ አማኞች ሁሉ በልሳን ሊናገሩ እንደሚወድ፤ ነገር ግን ከዚያ ይልቅ ትንቢትን ቢናገሩ እንደሚወድ፣ በልሳን ከሚናገር ይልቅ (ካልተተረጎመ)፤ ትንቢት የሚናገር እንደሚበልጥ ይነግረናል፡፡ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሊያስተምረን የፈለገው ዋነኛ ሃሳብ፤ እንደ ቤተክርስትያን ስንሰበሰብ ከራሳችን ይልቅ በቤተ ክርስትያን መታነጽ ላይ ማተኮር ይኖርብናል፡፡
6. ለመጀመሪያው ጥያቄ ቁ6 ላይ የሰፈረውን ያንኑ ማንበብ ይቻላል፡፡ ጳውሎስ በልሳን ለቆሮንቶስ ሰዎች ቢናገር የማይጠቅማቸው ምክንያት ምን እንደሚናገር ስለማይገባቸውና ስለማይታነጹበት ሲሆን ሌሎቹ ስጦታዎች ግን በተለያየ መንገድ ቤተ ክርስትያንን የሚያንጹ ስጦታዎች ስለሆኑ ይጠቅማቸዋል፡፡
7. በነዚህ ቁጥሮች ላይ ጸሃፊው የተጠቀመው የሙዚቃ መሳሪያን ምሳሌ በማድረግ ነው፡፡ የሙዚቃ መሳሪያው የሚያወጣው ድምጽ ቃማው የሚለይና የሚታወቅ ዜማ ሊያወጣ ያስፈልጋል ነው የሚለን፡፡ እኛም እንደዚሁ ከአንደበታችን ትርጉም ያለው ነገር እንዲወጣ የሚጠበቅብን ሲሆን፤ ያለበለዚያ ግን ለነፋስ እንደምንናገር ከንቱ መለፍለፍ ይሆንብናል ማለት ነው፡፡
8. ጳውሎስ ሃሳቡን ለመደገፍ የተጠቀመበት ሁለተኛው ምሳሌ ቋንቋ የሚለውን ሃሳብ በመጠቀም ነው፡፡ አንድ ሰው ሊያነጋግረኝ ከፈለገ በማውቀው ቋንቋ መጠቀም አለበት፤ ያለበለዚያ ግን ሲያወራ ቢውል ለእኔም ሆነ ለእርሱ አይጠቅመንም፡፡ የጳውሎስ ምክር የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ከጌታ ለመቀበል የምንለምን ከሆነ ቤተ ከራሳችን ይልቅ ክርስትያንን የሚያንጽ ስጦታዎች እንድንለምን ይመክረናል፡፡
9. ሊደረስ የሚችልበት ማጠቃለያ ሃሳብ፤ አጥብቀን የምንፈልገውና ከጌታ የምንለምነው ስጦታ ሌሎችን የምናንጽበት፣ የምናበረታታበትና የምናጽናናበት ዓይነት ስጦታ ሊሆን እንደሚገባው ነው፡፡

# ጥናት ሃያ ሰባት 1ኛ ቆሮ 14፡13-26 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በልሳን የሚናገረውን ሰው ጳውሎስ የሚመክረው መተርጎም እንዲችል እንዲጸልይ ነው፡፡ ይህንን ምክር የሰጠበት ምክንያት፤ በቁ12 ላይ ቤተ ክርስትያን የምትታነጽበትን ስጦታዎች እንዲፈልጉ በተናገረው መሰረት ይህም ሰው ልሳን ሌሎችን እንዲያንጽ ካስፈለገ መተርጎም ስለሚኖርበት ነው፡፡
2. በልሳን በምንጸልይበት ጊዜ መንፈሳችን እንደሚጸልይ፤ አዕምሮአችን ግን ያለ ፍሬ እንደሚሆን ይነግረናል፡፡ በመንፈስም በአዕምሮም መጸለይ፣ በመንፈስም በአዕምሮም መዘመር እንደሚቻል ከቁ15 እንማራለን፡፡
3. በአዕምሮ መጸለይና በአዕምሮ መዘመር አስፈላጊ ሆኖ የሚያየው፤ የምንጸልየውንም ሆነ የምንዘምረውን ሰምተው በስብሰባው ውስጥ የሚገኙት ምዕመናን አሜን ሊሉና ሊስማሙ የሚችሉበት ብቸኛ መንገድ በመሆኑ ነው፡፡ ስጦታዎች ሌሎች የሚገለገሉበት ወይም የሚታነጹበት እንጂ በእኛ ደስታና ስሜት ላይ መመርኮዝ እንደማይኖርበት ያስተምሩናል፡፡
4. ከአማኞቹ ጋራ ራሱን ያወዳደረው በልሳን መናገርን አስመልክቶ ነው፡፡ ምስጋናው እኔ እንደሚመስለኝ በዚህ ነገር ከእነርሱ በልጦ በመገኘቱ ሳይሆን፤ እነዚህ ሰዎች ልሳንን የመንፈሳዊ ብስለት መለኪያ አድርገው ስለሚገምቱ(ቁ20)፤ እርሱ በልሳን የሚናገር ሰው መሆኑ ተሰሚነቱን የበለጠ ያጠናክረዋል የሚል እምነት ነው ያለኝ፡፡
5. ሌላ ጳውሎስ የሚያወዳድራቸው ነገሮች፤ በልሳን መናገርንና በአዕምሮ መናገርን ነው፡፡ የሚበልጠው በአዕምሮ መናገር ነው፤ለዚህም ምክንያቱ ጳውሎስ ደጋግሞ እንዳስተማረው በቤተ ክርስትያን ውስጥ የሌሎች መማርና መታነጽ ዋነኛው ዓላማው አድርጎ ስለሚያምንበት ነው፡፡
6. ሕጻን ነገሩ የሚያስገኘውን ጠቃሚነት ሳይሆን የሚያብለጨልጭ፣ ለጊዜው ደስ የሚለውን ነገር የመምረጥ ዝንባሌን እንደሚያሳይ፤ የቆሮንቶስ አማኞችም ሌሎች አማኞች የሚማሩበትንና የሚታነጹበትን ስጦታ ሳይሆን ላይ ላዩን መንፈሳዊ በሚያስመስል ነገር ግን ለቤተ ክርስትያን ምንም ዓይነት ጥቅም በማይሰጥ ስጦታ ላይ መረባረባቸው የህጻን አስተሳሰብ እንደሆነ ሲያረጋግጥላቸው ነው፡፡
7. ሌላው በጉባኤ መሃል ልሳን እንዳንናገር የሚነግረን ሃሳብ የማያምኑ ሰዎች ወይም እንግዶች አብደዋል ሊያሰኛቸው ስለሚችል ነው፡፡ በዚህ ቦታ በልሳን ከመናገር ይልቅ ትንቢት መናገርን ሲያበረታታ እናያለን፡፡
8. አንደኛው ምክንያት ሌሎች አለመታነጻቸው ወይም አለመማራቸው ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ አዲሶች መሰናከላቸው ነው፡፡ እኔ እንደሚመስለኝ አብዛኛው ሰው ተቀብሎ እየኖረበት ያለውን ህይወት ልክ አይደላችሁም፤ አቁሙ፤ እውነቱ ይህ ነው ብሎ በድፍረት መናገር ትልቅ መስዋዕትነት የሚጠይቅ ነገር ስለሆነ ሁሉም እንዳላየ የሚያልፈው ነገር ይመስለኛል፡፡

## ጥናት ሃያ ስምንት 1ኛ ቆሮ 14፡27-40 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ምንባቡ ያተኮረባቸው የጸጋ ሥጦታዎች፤ ትንቢት መናገርና፣ በልሳን መናገር ናቸው፡፡ መዝሙር፣ ትምህርት፣ መግለጥ፣ በልሳን መናገር፣ በልሳን የተነገረውን መተርጎም ናቸው፡፡ ግልጋሎታቸው ለማነጽ እንደሆነ በገልጥ ተነገሯል፡፡
2. ልሳን የሚናገር ሰው ሲኖር ሁለት ቢበዛ ደግሞ ሶስት በየተራ እንዲናገሩ ሲደነግግ፤ ሎሎች ደግሞ ትርጉሙን እንዲናገሩ ይለናል፡፡ ተርጓሚ በሌለበት ጊዜ በጉባኤ መሃል ዝም እንዲል ደንግጓል፡፡
3. እነዚህ አነጋገሮች የትዕዛዙ ተፈጻሚነት እንደ ቤተ ክርስትያን ስንሰበሰብ መሆኑን ያረጋግጡልናል፡፡ በጉባኤ መሃል የማይተረጎም ቢሆንም በልሳን መናገርን እንደከለከለን ሆኖ አላየውም፤ የሚተረጉም ሰው ከሌለ ጉባኤው ሊታነጽ ስለማይችል ለሌሎች እንደሚናገር ሆኖ ሳይሆን ከእግዚአብሄር ጋራ እንደሚነጋገር በዝቅተኛ ድምጽ እንዲያደርገው ማለት ነው፡፡
4. እነዚህ ቁጥሮች ትኩረታቸው በትንቢት ስጦታ ላይ ነው፡፡ እነዚህ ቁጥሮች ልዩነታቸው አንዱ በልሳን ላይ ሲያተኩት ሌላኛው ደግሞ በትንቢት ላይ ያተኮረ ነው፤ ሌላው ልዩነት ደግሞ ሌላ በልሳን የሚናገር ካለ የእርሱ ስራ መተርጎም ከቻለ መተርጎም ሲሆን የማይተረጉም ከሆነ ግን ዝም እንዲል ነው ሲሆን ሌላ ነብይ ካለ ግን የእርሱ ስራ የተነገረውን ትንቢት መመዘን ነው፡፡ የነዚህ የሁለቱ ተመሳሳይነት ደግሞ ሁለቱም ከሁለት ወይም ሶስት በላይ ተናጋሪ እንዳይበልጥ መነገሩ ነው፡፡
5. እያንዳንዳችን እንድንማርና እንድንበረታታ ስለሚገባ፤ የነብያት መንፈስ ለነብያት መገዛቱና፤ ሌላው ደግሞ እግዚአብሄር የሰላም አምላክ እንጂ የሁከት አምላክ አለመሆኑ የሚሉት እንደሆኑ እመለከታለሁ፡፡
6. ምንም ዓይነት መንፈሳዊ ስጦታ አለኝ የሚል ሰው ቢኖር ይህ ጳውሎስ የሚያስተላልፈው መልዕክት ከጌታ እንደሆነ መቀበል እንደሚኖርበት ያሳስበናል፡፡ ይህ ማለት ይህንን መልዕክት የማይቀበል ነብይም ሆነ ማንኛውም ዓይነት መንፈሳዊ ስጦታ አለኝ የሚል ሰው እርሱ ራሱ በእግዚአብሄር ፊት ተቀባይነት አይኖረውም ማለት ይመስለኛል፡፡
7. እነዚህ ሁለት ቁጥሮች የሚመሳሰሉበት የማየው አንድ ነገር፤ ሁለቱም ትንቢት መናገርን በብርቱ እንድንፈልግ ያበረታቱናል፡፡ በቁ2-4 ውስጥ ትንቢት የሚናገር ቤተ ክርስትያንን ስለሚያንጽና፤ የመሰብሰባችን አንዱ ዓላማም ያ ስለሆነ ከዚህ የተነሳ የነገሩን አስፈላጊነት ስለተረዳ ይመስለኛል ይህንን ሃሳብ በመደጋገም ሊያሳስበን የመረጠው፡፡
8. በመጀመሪያ ደረጃ የተነገረው ነገር፤ በልሳን መናገር እንዳንከለከል፣ ሌላው ደግሞ ሁሉም በአግባብና በሥርዓት እንዲሆን ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ሃሳቦች የሚያያዙት በልሳን መናገር እንደማንከለከል ሁለቱም ክፍሎች የሚያረጋግጡልን ሲሆን፤ በአግባብና በሥርዓት የማድረግን ጉዳይ ደግሞ ስንመለከት በቁ28 ላይ የተሰጠንን መመሪያ ተከትለን ሥጦታችንን መጠቀም እንደሚኖርብን ሁለቱን ጥቅሶች በአንድነት በመመልከት መማር እንችላለን፡፡

# ጥናት ሃያ ዘጠኝ 1ኛ ቆሮ 15፡1-11 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በመጀመሪያ ደረጃ ጳውሎስ የሰበከላቸው ይህንን ወንጌል ነው፣ በሁለተኛ ደረጃ የተቀበሉት ይህንኑ ወንጌል ነው፤ ሶስተኛው ደግሞ፤ የቆሙበትም ይህ ወንጌል ነው፡፡ ትክክለኛ ደህንነት ማግኘታቸው የሚረጋገጥበት አንዱ መንገድ የተሰበከላቸውን ወንጌል አጥብቆ በመያዝ እንደሆነና ያለበለዚያ ግን እምነታቸው ከንቱ እንደሆነ ይናገራል፡፡
2. በ1ኛ ቆሮ 15፡2 ላይ ያሉት ሰዎች የደህንነታቸው ማረጋገጫ የተሰበከላቸውን ቃል አጥብቆ መያዝ መሆኑን የሚያረጋግጥ ክፍል ሲሆን፤ በዮሐ 8፡31-32 ላይ ያለው ክፍልም ኢየሱስ የሚናገራቸው በእርሱ ያመኑትን አይሁድ ሲሆን ደቀ መዝሙር የመሆናቸው ማረጋገጫ ከኢየሱስ የተማሩትን ትምህርት አጥብቆ መያዛቸው እንደሆነ ስለሚናገር ሁለቱ ክፍሎች የሚደጋገፉ ናቸው፡፡
3. ከነዚህ አነጋገሮች ወንጌል ተቀብለን እኛውጋ የምናስቀረው ነገር ሳይሆን ወደሌሎች መተላለፍ ያለበት ነገር እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ጳውሎስ በዚህ ቁጥር ላይ እንደሚናገረው ወንጌል ለእርሱ ከሁሉ ነገር በላይ እንደሆነ ነው፤ ለዚህም ነው ወደ ሌሎች ማስተላለፍ ለእርሱ አጠያያቂ ያልሆነበት፡፡
4. ጳውሎስ እንደ ወንጌል እውነት የጠቀሳቸው፤ ክርስቶስ ስለ ሃጥያታችን ሞተ፣ ተቀበረና በሶስተኛው ቀን ተነሳ፤ የሚሉት ናቸው፡፡
5. ክርስቶስ ከሙታን ለመነሳቱ የዓይን ምስክር ሊሆኑ የሚችሉ ቢያንስ 512 ሰዎችን እናያለን፡፡ ቁ8 ‹‹እንደ ጭንጋፍ ለምቆጠር›› ቁ9 ‹‹ከሐዋርያት ሁሉ ለማንስ›› ‹‹ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ›› ከሚሉት አነጋገሮች ይህ ሰው የተሰማውን ስሜት መረዳት ይቻላል፡፡
6. ጳውሎስ ቀድሞ ቤተ ክርስትያንን አሳዳጅ ነበረ፤ አሁን ግን ቤተ ክርስትያንን የሚመሰርት፣ የሚያጠናክርና የሚያነቃቃ የእግዚአብሄር ሃዋርያ ነው፡፡ በቁ10 እንደሚነግረን አሁን በህይወቱ እየተከናወነ ላለው ማናቸውም ዓይነት መልካም ነገር ሁሉ ተጠሪው የእግዚአብሄር ጸጋ እንደሆነ ግልጽ አድርጎ ይነግረናል፡፡
7. እግዚአብሄር ሥራውን እንድሰራ ጸጋውን ሰጥቶኛል፤ እኔም ደግሞ ጸጋውን በከንቱ የተቀበልኩ እንዳልሆን ስንፍናን ሳላሳይ በትጋት ሥራውን እሰራለሁ እንደሚል ነው የምረዳው፡፡ አንደኛው ሥራው ጳውሎስን ከነበረበት አንስቶ ዛሬ ላለበት እንዳበቃው የእኛንም ህይወት ዕለት በዕለት በመለወጥ የልጁን መልክ እስከንመስል ይሰራናል፤ ሌላው ደግሞ የሰጠንን አገልግሎት ለመፈጸም ብርታቱንና ጉልበቱን ሁሉ ያጎናጽፈናል፡፡
8. እዚህ ሥፍራ እየጠቀመ ያለው በተለይም በቁ3-4 ላይ ያለውን የወንጌል ማዕከላዊ መልዕክት የሆነውን የክርስቶስን ለሐጥያታችን መሞት፣ መቀበርና መነሳት ነው፡፡

# ጥናት ሰላሳ 1ኛ ቆሮ 15፡12-34 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እንደማይነጣጠሉ ያቀረባቸው፤ የክርስቶስን ከሞት መነሳትና፣ የቅዱሳንን ትንሳኤን ነው፡፡ በክርስቶስ ትንሳኤ ላይ የተንጠለጠሉት ሃሳቦች፤ ስብከታችን፣ እምነታችን፣ ምስክርነታችን የሚሉት ነገሮች ናቸው፡፡
2. በነዚህ ቁጥሮች እንደሰፈረው ትንሳኤ የክርስትና ምሰሶ ማለትም ክርስትና ያለትንሳኤ ሊቆም የሚችል ነገር እንዳልሆነ ግልጽ ያደርግልናል፡፡ ጳውሎስ መደምደሚያና ማጠቃለያ ሃሳብ አድርጎ የሚያስተምረው እውነት የሚገኘው በቁ20 ላይ ሲሆን፤ ይኸውም ‹‹ክርስቶስ ከሙታን ተነስቷል›› የሚል ነው፡፡
3. ከነዚህ ሁለት ቁጥሮች መገንዘብ የሚቻለው እውነት፤ ሞት ወደ እኛ የመጣው በአንድ ሰው በኩል እንደሆነ ሲሆን ትንሳኤም ደግሞ በአንድ ሰው በኩል እንደመጣ ነው፤ ከዚህም በተጨማሪ ሞትና ትንሳኤ ወደ እኛ የመጡትም አዳምና ኢየሱስ በተባሉት ሰዎች በኩል እንደሆነም እናነባለን፡፡
4. የትንሳኤ ቅደም ተከተል፤ በመጀመሪያ በኩራችን የሆነው ክርስቶስ ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ ደገሞ ጌታ ሲመጣ እኛ በእርሱ ያመነው እንነሳለን፡፡ ፍጻሜ የሚሆነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ግዛትን፣ ሥልጣንንና ሃይልን ሁሉ በመደምሰስ መንግስትን ለእግዚአብሄር አብ ሲያስረክብ እንደሆነ እናነባለን፡፡
5. ሞትን እንድንመለከት የሚፈልገው፤ ሌሎች የክርስቶስና የእኛ ጠላቶች ሁሉ እስከሚደመሰሱ ድረስ እስከ መጨረሻው የሚኖር ጠላት እንደሆነ እንድናይ ነው፡፡ ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጥ ያስፈለገው ነገር በቁ27 ላይ ‹‹ሁሉን ነገር ከእግሩ በታች አስገዝቶለታል›› የሚለው አነጋገር ሲሆን፤ ማስተካከያው ሃሳብ ይህ ‹‹ሁሉን›› የሚለው አባባል እግዚአብሄርን እንደማይጨምር መግለጽ ነበረ፡፡
6. በ1ኛ ቆሮ 5፡11 ላይ ርኩሰት በሞላበት አኗኗራቸው ሊበክሉን ከሚችሉ ሰዎች እንዲርቁ የሚናገር ሲሆን፤ በዛሬው ጥናት ማለትም በቁ32-33 ላይ ደግሞ በተሳሳተ ትምህርታቸው ሊበክሉን ከሚችሉ ዓይነት ሰዎች መራቅ እንደሚኖርብን እናነባለን፡፡
7. ዘወትር ለአደጋ መጋለጡን፣ በየቀኑ መሞቱ ማለትም በሥጋው እስከሞት ሊያደርሰው የሚችል ሁኔታ ውስጥ ማለፉ፣ ከአራዊት ጋራ መታገሉንና የመሳሰሉትን ነገሮች በሙሉ፤ ከፊቱ ትንሳኤ የሚባለውን ተስፋ ከልቡ ስለተቀበለው እነዚህን ሁሉ ነገሮች በጸጋና በደስታ ለመቀበል ችሏል፡፡ እያንዳንዱ የየራሱን መልስ ይስጥበት፡፡

# ጥናት ሰላሳ አንድ 1ኛ ቆሮ 15፡35-58 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የነዚህ ሰዎች ጥያቄ፤ ሙታን እንዴት ነው የሚነሱት? ሲነሱስ በምን ዓይነት አካል ነው የሚነሱት? የሚሉ ሲሆኑ፤ ጳውሎስ ለእነዚህ ሰዎች መልስ ለመስጠት እየተጠቀመ ያለው ዘርን በመጠቀም ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች አብዛኛዎቻቸው በግብርና የሚተዳደሩ ስለሆኑና ከአመት ወደ አመት እየዘሩ ዘሩ ሞቶ ፍሬ ሲያፈራ ማየት የተለማመዱ ሰዎች፤ ‹‹ሙታን እንዴት ይነሳሉ›› ሲሉ ዘርቶ ምርት መሰብሰብ ምን ማለት እንደሆነ ያላስተዋሉ ይመስላል፡፡
2. የተጠቀሱት ሶስት የሥጋ ዓይነቶች ሲሆኑ፤ እነርሱም የሰው፣ የእንስሳና የዓሳ ሥጋ ናቸው፡፡ ‹‹ክብር›› የሚለው ቃል ሲሆን ስድስቴ በቀጥታ ወይም ሰባት ማለትም ይቻላል፡፡
3. ሰማያዊና ምድራዊ አካልን የሚለየውን ነገር በአንድ ቃል ሲጠቃለል ‹‹ክብር›› እላለሁ፡፡ የሚዘሩባቸው አራቱ መንገዶች፤ የሚበሰብስ፣ በውርደት፣ በድካምና ፍጥረታዊ አካል ሲሆኑ፤ የሚነሳበት መንገድ ደግሞ የማይበሰብስ፣ በክብር፣ በሃይልና መንፈሳዊ አካል ይዞ ነው፡፡
4. ሁለት አይነት አዳሞች አያለሁ፡፡ አንደኛው አዳም የመጀመሪያው በመባል ይታወቃል፤ ሌላው ደግሞ የኋለኛው አዳም ይባላል፤ የመጀመሪያው ህያው ነፍስ ሲሆን የኋለኛው ህይወት የሚሰጥ መንፈስ፤ ቀድሞ የመጣው ፍጥረታዊው ሲሆን ከዚያ መንፈሳዊው መጣ፤ የመጀመሪያው ምድራዊ ሲሆን፤ የኋለኛው ሰማያዊ ነው፤ የምድራዊውን አዳም መልክ እንደለበስን፤ የሰማያዊውንም ሰው መልክ እንድንለብስ ያረጋግጥልናል፡፡
5. ሥጋና ደም የእግዚአብሄርን መንግስት እንደማይወርሱና፤ የሚጠፋው የማይጠፋውን እንደማይወርስ የሚሉት ናቸው፡፡ ምስጢሩ ሁላችን እንደማናንቀላፋ፤ ደግሞም ሁላችን እንደምንለወጥ ነው፤ ይህም የሚሆንበት ጊዜ የመጨረሻው መለከት ሲነፋ በቅጽበት ዓይን ነው፡፡
6. በቁ54 መሰረት የሚጠፋው የማይጠፋውን፤ የሚሞተው የማይሞተውን ሲለብስ ነው፡፡ ቁ57 እንደሚነግረን በክርስቶስ በኩል ድልን የሚሰጠን እግዚአብሄር እንደሆነ ነው የምንመለከተው፡፡
7. ይህ ቁጥር የጀመረው ‹‹ስለዚህ›› በሚለው ቃል ነው ሲሆን፤ ሊያያይዝ ያሰበውም ከላይ በቁ55-57 ከተናገረው ከሞት ድል መነሳትና እግዚአብሄር ለእኛ ለአማኞች በክርስቶስ በኩል በሞት ላይ ድልን ከመስጠቱ ጋራ ነው፡፡
8. በእምነት ጸንቶ መቆምን፣ በምንም ነገር አለመናወጥንና፣ ለጌታ ሥራ ዘወትር መትጋትን በአማኝ ውስጥ ሊያስገኝ ይገባል፡፡ በእያንዳንዳችን ህይወት ውስጥ ይህ የሞት በድል መዋጥና በትንሳኤ ድል አድርገን የመነሳታችን ጉዳይ ጸንተን ለመቆማችን፣ ላለመናወጣችንና ለጌታ ሥራ ደግሞ ትልቅ ትጋት ማሳየትን በህይወታችን ሊያፈራ ይገባዋል፡፡

# ጥናት ሰላሳ ሁለት 1ኛ ቆሮ 16፡1-24 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ‹‹እኔ በምመጣበት ጊዜ እንዳይሆን›› ሰው በመፍራት ወይም ልዩ ማሳመኛ መንገድ መጠቀም እንደማያስፈልግ፤ ‹‹ከእናንተ እያንዳንዱ›› የሁሉም ሰው ሃላፊነት እንደሆነ፤ ‹‹እንደ ገቢው መጠን›› ከአቅም በላይ ያልሆነ እንደገቢው መሆን እንደሚኖርበት፤ ‹‹በየሳምንቱ›› አንዴ አውጥተን በቃ ሳይሆን የሚቀጥል መሆኑ፤ ‹‹እየለየ ያስቀምጥ›› ለእግዚአብሄር የሚሰጠው የታወቀና የተወሰነ ሆኖ ከሌላው ገንዘብ ለይተን ማስቀመጥ እንደሚኖርብን እንማራለን፡፡ ለቆሮንቶስ ብቻ እንዳልሆነ የምናውቀው በቁ1 ላይ ይህንኑ ማሳሰቢያ ለገላትያም ቤተ ክርስትያን መስጠቱ ነው፡፡
2. ገንዘቡ ለታቀደለት ሁኔታ እንዲደርስ የጳውሎስ ዕቅድ፡ በመጀመሪያ ደረጃ ቤተ ክርስትያኒቱ የምታምናቸውን ሰዎች ትመርጣለች፣ ጳውሎስ የመሸኛ ደብዳቤ ጽፎ ከመልዕክተኞቹ ጋራ ይልካል፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ጳውሎስም ከመልዕክተኞቹ ጋራ አብሮ ይሄዳል ማለት ነው፡፡
3. ‹‹ዕቅድ መንደፍ›› ማለት ይቻላል፡፡ ሁለቱም ክፍሎች እቅድን የሚመለከቱ ሲሆኑ በሁለቱም ክፍሎች ላይ የምንመለከተው ጌታ ቢፈቅድ የሚለው ሃሳብ ማዕከላዊ ሥፍራ እንደተሰጠው እንመለከታለን፡፡ እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ እንዲናገር ጊዜ ይሰጠው፡፡
4. በኤፌሶን ከተማ ለመቆየት የወሰነበት ምክንያት፤ ትልቅ የአገልግሎት በር ስለተከፈተለትና በዚያ እድል ለመጠቀም ነው፡፡ ውሳኔውን ሊያሳጥፍ የሚችል ነገር የማየው ከበሩ ጋራ የተቃዋሚዎች መብዛትም አብሮ መምጣቱ ነው፡፡ ከዚህ መማር የምችለው፤ የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለማድረግ ስንታዘዝ ያለ ተቃውሞና ችግር መሆን እንደሚኖርበት የሚለው አመለካከት የተሳሳተ መሆኑንና ከዚያ ጋራ ደግሞ እንቅፋቶች እንዳሉ እያየንም የእግዚአብሄር ሃሳብ የሆነን ነገር ለማከናወን ከልባችን መጨከን እንደሚኖርብን እማራለሁ፡፡
5. ሁለቱ ትዕዛዞች፤ ያለ ፍርሃት እንዲቀመጥ እንዲያደርጉና፣ ማንም እንዳይንቀው የሚሉት ናቸው፡፡ ከነዚህ ጋራ የተመሳሰሉና ለጢሞቴዎስ ለራሱ የተነገሩት፤ 2 ጢሞ 1፡7 ላይ እግዚአብሄር የፍርሃትን መንፈስ እንዳልሰጠንና፤ በ1 ጢሞ 4፡12 ላይ ደግሞ ማንም ታናሽነትህን አይናቀው እያለ ይነግረዋል፡፡
6. ጳውሎስን ደስ ያሰኘው ነገር የእስጢፋኖስ፣ የፈርደነጥስና የአካይቆስ መምጣት ነበረ፡፡ እነዚህ ሰዎች ያደረጉት ነገር ጳውሎስ የጎደለውን ነገር አሟልተውለታል፡፡ጳውሎስ በፊሊ 4፡16-17 ከምናየው ምንም እንኳን ከችግሩ መላቀቁን የሚፈልገው ቢሆንም፤ ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ደስ የሚሰኘው ሰዎች በወንጌል መስበክ ተባባሪ ሲሆኑና የበረከት ተካፋዮች ሲሆኑ ማየት የእርሱ ደስታው ነው፡፡
7. ጳውሎስ ስለ እነዚህ ሶስት ሰዎች የሚመሰክረው ምስክርነት የእርሱንና የቆሮንቶስ ሰዎችን መንፈስ ያሳረፉ እንደሆኑ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ሰዎች መታወቅ ይገባቸዋል (deserve recognition) ይላል፡፡
8. በመጀመሪያ ደረጃ የሚነግረን በአካይያ የመጀመሪያዎቹ አማኞች እንደሆኑ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ ቅዱሳንን ለማገልገል ራሳቸውን የሰጡ ሰዎች እንደሆኑ ነው፡፡ በቁ16 ላይ የሚለምናቸው እንደ እስጢፋኖስ ቤተሰዎች የመሰሉትን ሰዎች እንዲታዘዟቸው ነው፤ ምክንያቱም በአገልግሎት ስለሚደክሙ ነው፡፡